www.zeyeneta.com

ትምህርተ ውግዘት

(በአጭሩ)

አድራሻ፡- ዲያቆን ኅብረት የሺጥላ

ስልክ 251 091 1 617077
የመ.ሣ.ቁ 57133
E-mail address
Hibretyes@yahoo.com

www.zeyeneta.com

ትምህርተ ውግዘት

በዲያቆን ኅብረት የሺጥላ
ልኛ ኅትም ነሐሴ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!

© ALL RIGHTS RESERVED.

መታሰቢያነቷ

ከግማሽ ምእት ዓመት በላይ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው በቅርቡ ላረፉት ለአለቃ አያሌው ታምሩ ትሁንልኝ!

ምስጋና

ረቂቁን በማንበብ ገንቢ አስተያየትና እርማት ለሰጡኝ ለቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ፣ ለዲያቆን ሄኖክ ኃይሌና ለወጣት ዘመድኩን ተሾመ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ምዕራፍ አንድ

- መቅድም ..... ፩-፯
- ውግዘት ምንድር ነው? ..... ፯-፲፬

ምዕራፍ ሁለት

- ማውገዝ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘብ ስለመሆኑ ..... ፲፫-፲፯
- የማውገዝ ሥልጣን ለካህናት በጸጋ ስለመሰጠቱ ..... ፲፯-፲፰

ምዕራፍ ሦስት

- ሥልጣነ ክህነት ከውግዘት አንጻር በኦሪትና በአዲስ ኪዳን ..... ፲፱-፳

ምዕራፍ አራት

- ውግዘት የሚያስከትለው ጉዳት ..... ፳፩-፳፯

ምዕራፍ አምስት

- ከማውገዝ በፊት ስለመታገሥ ..... ፳፯-፴፩

ምዕራፍ ስድስት

- ስለ ‹‹ከንቱ ግዝት›› ..... ፴፪-፴፭
- ከንቱ ግዝት ወደራስ ስለመመለሱ ..... ፴፭-፴፱

ምዕራፍ ሰባት

- ውግዘትን ስለመፍራት ..... ፴፫-፴፱

ምዕራፍ ስምንት

- በዝምድና፣ በጥቅም፣ በባልንጀርነት እየተደለሉ፣ በኃይል እየተገደዱ ስለማውገዝና ስለመወገዝ ..... ፵-፵፬
- መወገዝ ያለበትን ሳያወግዙ ስለመቅረት (ስለቸልተኝነት) ..... ፵፭-፵፯
- ውግዘትን ስለሚያስከትል የዓመፅ ዓይነት ..... ፵፯-፶፬
- ማጠቃለያ መልእክት ..... ፶፬-፶፪
- ዋቤ መጻሕፍትና ሌሎችም ..... ፶፪-፶፬

www.zeyeneta.com

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

መቅድም

ይህች አነስተኛ መጽሐፍ ስለ ውግዘት ምንነትና ምሥጢር አብራርታ የምታስረዳ በመሆኗ ‹‹ትምህርተ ውግዘት›› ተብላ ተሰይማለች። ምክንያተ ጽሕፈታ በቅርቡ በመገናኛ ብዙኀን ከተለያየ አቅጣጫ ስንሰማው የነበረው መወጋገዝ ነው።

በበቂ ሁኔታ ባላወቁት ነገር ላይ አስተያየት መስጠት ሌሎችን ያሳስታል፣ ከተሳሳተ መደምደሚያም ያደርሳል፣ ብዙዎችንም ቅር ሊያሰኝ ይችላል። በመጨረሻም ኃጢአት ሆኖ ከፈጣሪ ዘንድ ወቀሳና ከሰሳ ያስከትላል። ስለዚህ አዘጋጁ ከሐሜት ይልቅ የልቡን ስጋቱ ለመቀነሥ የሚረዳውን አስተማሪ መጽሐፍ ለመጻፍ ወስኗል።

በጊዜያችን ስላለው መወጋገዝ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል በቂ የታሪካዊም ሆነ የነባራዊ ሁኔታዎች ማስረጃ ያላቸው ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ አእምሮው ጥያቄ የማያጭርበት፣ ልቡ በመንፈሳዊ ቅናት የማይናጥበትና የማይፈተንበት ምእመን አይገኝም።

ይህን በመሰለ ጊዜ መናፍቃንም አርፈው እንደማይተኙ እናውቃለን። በዓሥራ ዘጠኝ ሰማንያዎቹ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ሳለ ልዩ ልዩ ጋዜጦች ለንግድ ብለው ጉዳዩን ሲያራግቡ መናፍቃን ደግሞ በበኩላቸው ክፍተቱን ለመጠቀምና ምእመናንን ለማደናገር ‹‹እውነተኛ ሰላም የሚገኘው የት ነው?›› በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀ ጠማረ ሞት (የሞት በራሪ መልእክት) አሰራጭተው ነበር።

በአጠቃላይ በዚህ ዓይነት ወቅት ምእመናንን የሚያደናግሩ ሰዎች ይነሡና በርካታ ውዥንብር ይፈጥራሉ። በቅርቡ የተፈጠረውን መወጋገዝ ተከትሎ ከተፈጠሩ የክህደት ዓይነቶች አንዱን ለምሳሌ ያህል መጥቀስ እፈልጋለሁ። ይኸውም በአንድ የመረጃ መረብ ድኅረ ገጽ ላይ ራሳቸውን ገለልተኛ አድርገው የሚቆጥሩ አንድ ካህን ተጠይቀው የሰጡት መልስ ነው። እኚሁ ካህን ‹‹ኃጢአትን ለካህን በመንገር መናዘዝ ተገቢ ሥራ ነው›› ካሉ በኋላ ‹‹ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት አባቶቻችን እርስ በእርሳቸው ስለተወጋገዙና ካህንነታቸው ስለቀረ ወደ ሊቀ ካህናችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናዘን ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ እንችላለን።›› በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ይህንን ገለጻ በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛንነት ስንመለከተው ከባድ ክህደትና እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሆኖ እናገኘዋለን። አስቀድመው ‹‹ሁሉም ተወጋግዘዋል ካህን የለም።›› ካሉ በኋላ ለሊቀ ካህናታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን ተናዘን እንቀርባለን።›› ማለት ምን ማለት ነው? ካህናት ከሌሉ የሚያቆርበንስ ማን ነው? ወይስ የማናዘዝ ሥልጣንና ቀድሶ የማቁረብ ሥልጣን የተለያየ ነውን? ለማናዘዝ የማይበቁ ከሆነ ቀድሰው ሊያቆርቡ እንደምን ይችላሉ?

ለሊቀ ካህናታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንናዘዛለን ማለትስ ከምሥጢረ ንስሐ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ አይጋጭምን? በዚህ አጋጣሚ ይህን የመሳሰሉ የመናፍቃን የክህደት ትምህርቶች በግርግር ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ ያሰጋል። ንስሐን አስመልክቶ መናፍቃንም የሚያስተምሩት ይህንኑ ነውና።

የተወደዳችሁ ምእመናን ሆይ! እስኪ እናንተ ፍረዱ ሁለት ካህናት በምንም ምክንያትና መንገድ ቢወጋገዙ ሊሆን የሚችለው ምንድር ነው? አንዱ ሌላውን በእውነት ቢያወግዘው ሌላኛው ደግሞ መልሶ በቁጣ ቢያወግዘው ለእኛ የተወጋገዙ ይምሰሉን እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደዚያ አይደለም። ተፈጻሚ የሚሆነው በእውነት ያወገዘው ካህን ውግዘት ብቻ ነው። ስለዚህ የጥፋተኛው ካህን ክህነቱ ሲታሰር የእውነተኛው አውጋዥ ክህነት እንዳለች ትቀራች ማለት ነው።

አንዱ በሐሰት አስቀድሞ ቢያወግዝ ሌላኛው ደግሞ ቀጥሎ በሚገባ መንገድ አውጋዡን ቢያወግዘው ቅደም ተከተሉ የሚፈጥረው ችግር የለም። እውነተኛ አውጋዥ የሆነው ካህን ሹመቱ የተጠበቀች ናት። ሐሰተኛው ግን ቀድሞ ቢያወግዝም በሚገባ አይደለምና ውግዘቱ አይሠራለትም። እርሱ በሚገባ ሲወገዝ ግን ክህነቱ ትያዛለችና የክህነት ሥልጣን አይኖረውም።

ሁለት ካህናት እርስ በእርስ ተወጋግዘዋልና ክህነት የላቸውም ማለት እጅግ ትልቅ ስሕተት ነው። ውግዘትን በሕያው እግዚአብሔር የማይመራና ሄዶ እንደሚጋጭ ግዙፍ ነገር እንደ መቁጠር ይሆናል። ሁለት ካህናት እርስ በእርስ ሲወጋገዙ የሁለቱም ክህነት የሚሻርበት ወይም የሚታሰርበት ምንም ዓይነት አካሄድ የለም።

www.zeyeneta.com

አባቶቻችን ስለተወጋገዙ ‹‹በሁለቱም ወገን ሥልጣነ ክህነት የለም›› የሚሉ ሰዎች እኛ ገለልተኛ ነንና እውነተኛ ክህነት ያለው እኛ ዘንድ ብቻ ነው ለማለት ይሆን? አባቶቻችን እርስ በእርስ ሲወጋገዙ የሁለቱም ወገን ክህነት የተሻረ ከሆነ ሁለቱም ወገኖች ተጸጽተው ይቅርታ ቢጠያየቁ ክህነታቸው ተመልሶ ከየት ሊመጣ ይችላል? እርስ በእርስ ሲፈታቱ ነውን? መቼም ይህ ሊሆን አይችልም። የተወገዘ መፍታት አይችልምና። ተወግዞ መፍታት ከቻለ ግን መወገዙ ምኑ ላይ ነው አያሰኝምን?

ይህን ከመሰለው የክህደት ፈጠራ በተጨማሪ ጉዳዩን አስመልክቶ ምእመናንን የማያንጹ ሸካራ ስብከቶች ይሰማሉ፣ ጠማማ ጽሕፈቶችም ይነበባሉ። ጉዳዩን የሚያባብሱ፣ ተስፋ የሚያስቆርጡና ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ የሚያሳንፉና ልዩ ልዩ ፈተናዎች በሕሊና እንዲመላለሱ የሚያደርጉ ነገሮች በየጊዜው ይናፈሳሉ። ይህን የመሰለ መጽሐፍ መጻፍ ያስፈለገውም ይህን መሰሉን የኃጢአት ጎዳና ሁሉ ለይቶ ለማሳየትና ምእመናንን ለማስጠንቀቅ ነው።

መናፍቃን በዚህ ዓይነት ጊዜ በዘመቻ ሥራ ክህደታቸውን ለመዝራት እንደሚጣደፉ ይታወቃል። ስለዚህ ምእመናን በእምነታቸው እንዲጸኑና ግራ እንዳይጋቡ ከማሰብ በወቅቱ በየዓውደ ምህረቱ ሳካፍል የነበረውን ትምህርት በእውነት ያለ ሐሰት በምእመናን ቀስቃሽነትና አነሣሽነት በዚህ መልኩ በጽሑፍ አዘጋጀሁት።

የመጽሐፉ ዋና ዓላማ በተፈጠረው ችግር ምእመናን እንዳይታወኩ ማረጋጋት፣ በሃይማኖት እንዲጸኑ፣ በሐሜትና በሰው በመፍረድ እንዳይጎዱ በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። በተጨማሪም አንዳንድ ሰዎች ስለውግዘት ያላቸው ጭብጥ የተዛባ ስለሆነ ያንን ማቃናትና ሚዛናዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ስለዚህ ውግዘትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ምን እንደሆነ በዚህ መጽሐፍ ተብራርቶ ቀርቧል። ስለውግዘት ሸሐሜት፣ ከአሉባልታና ከግል ስሜት የጸዳና ከጠራ ምንጭ የተቀዳ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሐሊበ ትምህርት የተጠማ ሰው ያንብባት!

‹‹አቤቱ ጽዮንን አስባት››

ጸሐፊው

ምዕራፍ አንድ

ውግዘት ምንድር ነው?

ውግዘት ‹‹ወገዘ›› ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን የተለያዩ አገባቦችና ፍቺዎች አሉት። ፍቺዎቹን በተናጠል መመልከት ፅንሰ ሐሳቡን የበለጠ ለመረዳት ይረዳል።

፩ መለየት

ማውገዝ ጥፋተኛ አካልን መለየት የሚል ፍቺ አለው። ይኸውም ከቤተ ክርስቲያን፣ ከጉባኤ እግዚአብሔር ከምሥጢራተ እግዚአብሔር ማለትም ከቅዱስ ቁርባንንና ከመሳሰለው ሁሉ እንዲለዩ ማድረግ ማለት ነው። ይህን ሲያስረዳ ሃይማኖተ አበው ‹‹በውግዘት የተለየ›› ይላል።

ማውገዝ መምተር፣ መቁረጥ ማለትም ይሆናል ‹‹የሚያውኩአችሁ ይቆረጡ›› እንዲል። (ገላ፭÷፲፪) በዚህ ስፍራ ‹‹ይቆረጡ›› የሚለው ቃል አቻ ትርጉሙ ‹‹ይለዩ›› ማለት እንደሆነ ግልጥ ነው። ለመቁረጥ የመቁረጫ መኖር ግድ ነው። ኢአማንያንን፣ መናፍቃንንና ክፉዎችን ከምእመናን የሚለይ መንፈሳዊ መቁረጫ ደግሞ ውግዘት ነው።

ውግዘት መንፈሳዊ ሰይፍ ነውና ኢአማንያንን ከአማንያን ይለያቸዋል። ይሁን እንጂ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ***‹‹ወኢንመልሕ ሰይፈ በላዕሌክሙ። አላ ናስተሐምም ለመድኃኒትክሙ››*** ፤ ‹‹እንድትድኑ ወደን እንታገሣችኋለን እንጂ በእናንተ ላይ ቸኩለን ሰይፋችንን አንመዝዝም። (ፈጥነን አናወግዛችሁም)›› ብሎ እንደጻፈው ይህ እጅግ ስለታም የሆነ መንፈሳዊ ሰይፍ ትዕግሥት በማጣት በየቦታው ያለአግባብ የሚመዘዝ መሆን የለበትም። ትዕግሥትና በቂ

www.zeyeneta.com

መንፈሳዊ ዕውቀት በሌለው ሰው እጅ ያለች ሥልጣነ ክህነት በአብድ እጅ እንዳለች ሰይፍ ናት።

በቅዱስ ወንጌል ከዚህ በታች ያለው ቃል ሰፍሯል። ‹‹እነሆም ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ጆሮውን ቆረጠው በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው፡ ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ።›› ይህ የሆነው አይሁድ ይገድሉት ዘንድ ጌታችንንና አምላካችንን እንደ ወንበዴ በያዙበት ጊዜ ነው። (ማቴ፳፮÷፶፩-፶፪)

አስቀድሞ እንደተገለጠው ሰይፍ ሥልጣነ ውግዘትን ያሳያል። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ለፈጣሪው ቀንቶ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ ቀኝ ጆሮ መቁረጡ ምሥጢር ነበረው። በዘመነ አሪት ከነገደ ይሁዳ የተወለዱ ቀኝ ቀኝ አካላቸውን እየተቀቡ መንግሥትን ከነገደ ሌዊ የተወለዱ ደግሞ ቀኝ ቀኝ አካላቸውን ተቀብተው ክህነትን ገንዘብ ያደርጉ ነበር። የጭፍራው ቀኝ ጆሮ በሰይፍ መቆረጡ ክህነትና መንግሥት ከአናንተ አለፉ ወይም ተወሰዱ የሚል አንድምታ ነበረው። የሥልጣናት ሁሉ ባለቤት የሆነውን ፈጣሪያቸውን ተቃውመውታልና። (ማቴ፳፮÷፶፩-፶፪ ትረጓሜውን ተመልከት)

ውግዘት መለየት ማለት መሆኑን የሚያስረዱ የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች እንመልከት። እስራኤላዊያን ወደጠሩት ጉባኤ ያልመጣውንና በውሳኔያቸው ያልተስማማውን ሰው ንብረቱ ሁሉ እንዲወረስና ከጉባኤ እንዲለይ እንዲህ ብለው አዋጅ ነግረዋል። ***‹‹ወኪያሁኒ ያውግዘም እምነ ማኅበሩ።››*** ይህ ቃል በመጽሐፈ ዕዝራ

ላይ የተጠቀሰ ሲሆን ‹‹እርሱንም ከማኅበሩ ይለዩት።›› ማለት ነው። (ዕዝ፲÷፰ ግእዙን ተመልከት)

በቅዱሳት አዋልድ መጻሕፍት በብዙ ስፍራ ***‹‹ብእሲ ዘአውገዘ ኤጲስ ቆጶስ››*** የሚል ሐረግ ይገኛል። ይህም ‹‹ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ በግዝት የለየው ሰው ቢኖር›› እንደ ማለት ነው። እንደዚሁም ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ›› ሲል ማውገዙና መለየቱ እንደሆነ ይታወቃል። (፩ቆሮ፭÷፪)

በሌላም ስፍራ ***‹‹አውገዝዎሙ እስከ ዛቲ ዕለት››*** የሚል ወረፍተ ነገር እናነባለን። ይህም ‹‹እስከዚች ዕለት ድረስ ለዩዋቸው›› የሚል አቻ ፍቺ አለው። በእነዚህ ሁሉ ምስክሮች የምንረዳው ማውገዝ መለየት የሚል ፍቺ እንዳለው ነው። ይህ ዓይነት አገባብ በፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ በሃይማኖተ አበውና በአብጥሊስ ቡተደጋጋሚ ተጠቅሶ ይገኛል።

፪ መካድ

ማውገዝ መካድ የሚል ትርጉም አለው። ይህም በዲድስቅልያ ላይ ሰፍሮ ከሚገኝ ቃል ይታወቃል። ቃሉም ***‹‹ዘይፈቅድ ይጠመቅ ይምሀርዎ ያውግዝ ሰይጣነ ወይእመን በክርስቶስ።››*** የሚል ነው። የአማርኛ አቻው ‹‹ሊጠመቅ የፈቀደውን ሰው ሰይጣንን እንዲክድና በክርስቶስ እንዲያምን ያስተምሩት።›› የሚል ነው። (ዲድስ፴፱)

የላይኛውን የመሰለ ***‹‹አወግዘከ ሰይጣን ወኩሉ ምግባራቲከ››*** የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን በአማርኛ ‹‹ሰይጣን ሆይ አንተንና ሥራህን ሁሉ እክዳለሁ›› ማለት ሲሆን በዘወትር ጸሎት ‹‹እክሀደከ ሰይጣን›› ከምንለው ጋር አንድ ዓይነት ነው። ይህም ማውገዝ መካድ መሆኑን ያስረዳል።

www.zeyeneta.com

፫ መርገም

ማውገዝ መርገምም ይሆናል። ስለቅዱስ ቶማስ በተጻፈ አርኬ ላይ ‹‹ለክይሲ ሶበ አውገዞ›› የሚል ሐረግ እናገኛለን። ይህም ስ ቶማስ ‹‹ከይሲ ዲያብሎስን በረገመው ጊዜ›› እንደማለት ነው። (ስንክ የካ፪)

በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ ‹‹ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው ቢኖር የተረገመ ይሁን።›› ያለውን ዲያቆኑ በቅዳሴ ጊዜ መልእክታትን ከማንበቡ በፊት ‹‹ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የተለየ (የተወገዘ፣ የተረገመ) ይሁን።›› ይላል። ‹‹በከመ ይቤ ጳውሎስ ውጉዘ ለይኩን›› እንዲል። (ቈቀሮ፲፮÷፳፪፤ መጽ፡ቅዳ) ይኸው ሐዋርያ በሌላ ስፍራ በተመሳሳይ አገባብ ‹‹ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።›› ብሏል። (ገላ፩÷፱)

በጌታችንና በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ልዩ ልዩ የክህደት ትምህርት አንቅተው ያስተማሩ መናፍቃን ላይ የቤተ ክርስቲያን አርምጃ ምን እንደሆነ ሃይማኖተ አበው አስረድቷል። በዚህም መግለጫው ላይ ከላይ የተዘረዘሩትን የውግዘት ፍቺዎች ተካተው እናገኛቸዋለን። ኃይለ ቃሉም የተጠቀሱትን መናፍቃን ቤተ ክርስቲያን ‹‹ታወግዞሙ፣ ወትረገሞሙ፣ ትፈልጦሙ፣ ወትመትሮሙ።›› የሚል ነው። ፍቺውም ቤተ ክርስቲያን ታወግዛቸዋለች፣ ትረግማቸዋለች፣ ቆርጣ ትለያቸዋለች ማለት ነው። (ሃይ አበ ምዕ፲፯÷፲፱-፲፭)

፬ መከልከል ማቀብ

ማውገዝ ማለት ማንኛውንም ነገር ከማሰብ ከመናገርና ከማድረግ መከልከል፣ ማቀብ፣ ሕርም ማድረግ የሚል ፍቺ አለው።

ለምሳሌ ‹‹ሲጋራ ማጨስ የተወገዘ ነው!›› ቢባል የተከለከለ ነው ለማለት እንደሆነ ማንም አይጠፋውም።

ይህን የመሰለ አንድምታ ያለው ቃል በፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ላይ ይገኛል። ቃሉም ‹‹ቀቲልሰ እምኀልቆ ዐበይት ኃጣውኢ ክሉኣት ወውጉዛት በልብ ወበሕግ።›› የሚል ነው። ትርጉሙም ‹‹መግደል ግን በልብና በሕግ ፍጹም ከተከለከሉ ታላላቅ ኃጢአቶች ቁጥር የሚመደብ ነው።›› ማለት ነው። (ፍት፡ነገ፡፶፮) ከላይ ለሰፈሩት ሐሳቦች ከሞላ ጎደል የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ እንደ ሁለተኛ ምንጭነት ይጠቀሳል።

፭ መፍረድ

ለሐዋርያት የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ከፈጣሪ ዘንድ ተሰጥቷቸዋል። ይህም እስከ ኅልፈተ ዓለም ድረስ ለሚነሡ ካህናት የሚሠራ እንጂ በእነርሱ ብቻ ተወስኖ የቀረ አይደለም። ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ‹‹እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የለው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ›› ብሏቸዋል። (ማቴ፲፱÷፳፰)

ስለዚህ ሐዋርያት በምድር የፈረዱት ፍርድ በሰማይ አይገሠሠባቸውም። ማለትም በሥልጣነ ክህነታቸው በምድር ላይ የሠሩት ማንኛውም ዓይነት ሥራ፣ ውሳኔና ፍርድ በዳግም ምጽአት ይጸናል ማለት ነው። ይህም ‹‹በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል›› በማለት ፈጣሪ ከሰጣቸው የማሰርና የመፍታት

www.zeyeneta.com

(የማውገዝ) ቃል ኪዳን ጋር የሚዛመድ ነው። (ማቴ፲፮÷፲፱) ማውገዝ መፍረድ ነው ያሰኘውም ይህ ምሥጢር ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ‹‹የፈረድነውን ፍርድ፣ ያወገዝነውንም ውግዘት›› ለማለት ***‹‹ወዘፈታሕነ ኩነኔ ፍትሕ ወዘአሠርነሂ››*** ብሏል። (ተግ ዘዮሐ አፈ፬) ይህም ውግዘት ፍርድ ይባላል ለተባለው ማስረጃ የሚሆን ቃል ነው።

በተጨማሪም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ ‹‹የአባቱን ሚስት ያገባውን›› ሰው አውግዞ ሲለይ ‹‹እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱሽ ክርስቶስ ስም አሁን ***ፈርጀበታለሁ።››*** ዳግመኛም ‹‹እንደዚህ ያለው ሰው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው›› በማለት ደጋግሞ የተናገረው ቃል ማውገዝ መፍረድ መሆኑን ያሳያል። (፩ቆሮ፭÷፬-፭)

ማውገዝ መወሰን፣ ማሰር፣ ሥርዓት መሥራት የሚል ትርጉምም አለው። የተሳሳተ እምነትንና ትምህርትን ይህ ሐሰት ነው ብሎ ‹‹ማሰር›› ይህ ደግሞ እውነት ነው ብሎ ‹‹መፍታት›› የማውገዝ ሥልጣንን የሚያሳይ ነው። ሰይጣንንና ሠራዊቱን ኃይል ማሳጣትና ማሰርም የማውገዝን ሥልጣን ያመለክታል። በአጠቃላይ ለማስረዳት በሚረዳ መልኩ ትርጉሙን ካልወሰነው በቀር ማውገዝ የሚለው ቃል በዘይቤ፣ በአገባብም ሆነ በምሥጢር ከዚህ በላይ በርካታ ፍቺዎች ሊኖሩት ይችላል።

ማውገዝ አጥፊውን ሰው በሥጋውና በነፍሱ ማሰር፣ መንፈሱን መግታት፣ ትምህርቱንና መጻሕፍቱን መከልከል ነው። እንዲህ ባለ ክፉ ሰው ላይ አድሮ የሚሠራውንም ርኩስ መንፈስ መቃወምና ማድከም ሐሳቡና እቅዱ፣ የሰውዬም ጠማማ እምነት ፍሬ ቢስ እንዲሆን ማድረግ ነው። ሰውዬው ቢሞት እንኳን ያደረበት

መንፈስ የሚሞት አይደለምና የዘራው ክፉ ዘር እንዳያፈራ ማገድ የውግዘት ዓላማ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ አርጌንስ ከሞተ ከ፪፻፶፬ በኋላ ከነመጻሕፍቱ ባልተወገዘም ነበር።

ሰው ሥራው ተመርምሮ ሲደረስበት ክፉ ሆኖ ከተገኘ ከሞተ በኋላም ሊወገዝ ይችላል። ለዚህ ሐሳብ አስረጅ እንዲሆን የአርጌንስን ታሪክ መጥቀስ ብቻ በቂ ነው። አርጌንስ ከ፪፻፲፭ እስከ ፪፻፶፬ ድረስ የነበረ መናፍቅ ነው። እርሱ ከሞተ ከ፪፻፶፬ ዓመት በኋላ በ፭፻፷፫ ዓም በቀዳማዊ ጁስቲኒያን ዘመነ መንግሥት በቁስጥንጥንያ በተደረገው ጉባኤ ከነመጻሕፍቱ ተወግዟል። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፶፮)

፮. መግደል

ከላይ ለውግዘት ከተሰጡት መንፈሳዊ ማብራሪያዎች አንጻር ከተመለከትነው ማውገዝ ማለት የአንድ ሰው ክፉ ማንነት ወደ ሌሎች እንዳይዛመት መንፈሳዊ ሩጫውን መግደል ማለት ነው። ከላይ ስለውግዘት በተሰጠው ትንታኔ መሠረት አንድ ሰው ከማኅበረ ምእመናን ከተለየ፣ ከተረገመ፣ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ካጣ ወይም ከተካደ፣ ከተፈረደበት ሞተ፣ ተገደለ ቢባል ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም።

የሞት ዋና ፍቺ መለየት ማለት እንደሆነ ሁሉ መግደል ሲባልም አንድን ሰው ለነፍሱና ለሰማያዊ ቤቱ ከሚያስፈልጉት መንፈሳዊ ነገሮች በሙሉ እንዲነጠል ማድረግ ማለት ነው። በዚህ ስፍራ ለውግዘት የተሰጠው መግደል የሚለው ፍቺ በሥጋ መግደልን በጭራሽ አያመለክትም። ከመሥራቿ ከኢየሱስ ክርስቶስ አንሥቶ ቤተ ክርስቲያን በሥጋ ስትገደል ኖራለች እንጂ ገድላ አታውቅም። የሚገድሉ ሁሉ ቁጥራቸው ከቤተ ክርስቲያን አይደለም።

www.zeyeneta.com

ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሥልጣኗ ግን ብዙዎችን ገድላለች ማለትም አውግዛ ለይታለች። ይህንንም ከዚህ በታች የሰፈረው ቃል ያስረዳናል። ሃይማኖተ አበው *‹‹ወበ አምኔሆሙ ዘትቀትሎሙ ቤተ ክርስቲያን››* ይለናል። ‹‹ዘትቀትሎሙ›› ማለት ‹‹የምትገድላቸው›› ማለት ስለሆነ ዐረፍተ ነገሩ ያለ ምንም ምሥጢር በጥሬ ሲፈታ ‹‹ከእነርሱም መካከል ቤተ ክርስቲያን የምትገድላቸው አሉ።›› የሚል ይመስላል። ይሁን እንጂ መግደል የሚለው ቃል በውግዘት መለየት ማለት ስለሆነ ትክክለኛ ትርጉሙ ‹‹ቤተ ክርስቲያን በውግዘት የምትለያቸው አሉ።›› የሚል ይሆናል። (ሃይ.አበ.ዘሠለስቱ ምዕት ምዕጽቁ፲፩) ማውገዝ መግደል ይባላል የተባለው ከዚህ አንጻር ነው። በተጨማሪም ሲወገዙ በቅሥፈት ሞት የሞቱ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኃይልና ሥልጣን የተገለጠባቸው ናቸው።

ሰዎች ምንም ያህል ስለ ሃይማኖታቸው ቢቀኑና ቢቆረቆሩ በዚህ ምክንያት ተነሣሥተውና ኃይለ ሥጋቸውን ተጠቅመው በሌላው ሰው ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ ይህ ተቆርቋሪነታቸው በፈጣሪ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ እጅ በተያዘ ጊዜ ስለ ፈጣሪው ቀንቶና ተቆርቁሮ የአንዱን ጭፍራ ጆሮ በሰይፍ በመቁረጡ ተገሥጿል እንጂ አልተመሰገነምና። እውነተኛ ተቆርቋሪነት የእኛን (የሥጋና የደማችንን) ፈቃድ መፈጸም ሳይሆን የምንቆረቆርለትን አካል (የእግዚአብሔርን) ፈቃድ መፈጸም ነው። ቤተ ክርስቲያን ዓመፀኞችን ስትቀጣ የምትጠቀመው ሥጋዊ ኃይልን ሳይሆን የማውገዝ ሥልጣኗን ነው። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ይህ ነውና።

ምዕራፍ ሁለት

ማውገዝ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘብ ስለመሆኑ

ከላይ እንደተብራራው ማውገዝ ማለት መለየት፣ መካድ፣ መርገም፣ መፍረድ፣ ማሰር፣ መወሰንና ሥርዓት መሥራት የሚል ትርጉም ካለው ይህን ለማድረግ ሥልጣን ያለው ብቸኛ አካል እግዚአብሔር መሆኑ አያጠያይቅም። በመጀመሪያ ማውገዝ ለእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው። ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነጥቦች ማውገዝ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘብ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው።

ትእዛዙን ባፈረሰ ጊዜ አዳምን ከገነት፣ ከመላእክት፣ ካለደረበት ጸጋ ሁሉና ከራሱም ሳይቀር የለየው እግዚአብሔር ነው። ማውገዝ መለየት ነውና። ‹‹ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን›› ብሎ እንኳን እርሱ የእርሱ የሆኑ ሁሉ የተረገሙ እንዲሆኑ አዳምን ያወገዘውም እርሱ ነው። ማውገዝ መርገምም ይሆናልና። (ዘፍ፫፥፲፯)

ማውገዝ መካድ ነው። ሐዋርያው ‹‹ብንክደው እርሱ ደግሞ ይክደናል›› እንዳለው አዳም ቢክደው ልጅነቱን የካደው እርሱ እግዚአብሔር ነው። ጌታም በወንጌል ‹‹በሰው ፊት የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።›› ብሎ

www.zeyeneta.com

አስጠንቅቆናል። (፪ጢሞ፪÷፲፫፣ ማቴ፲÷፴፫) ሥርዓት የሠራ፣ የወሰነ፣ ያሰረ፣ የታሰረውንም የፈታ፣ የሚዘጋ፣ የሚከፍት፣ እግዚአብሔር ነው። ይህ ሁሉ ደግሞ የውግዘት ምሥጢራዊ ፍቺ በመሆኑ ማውገዝ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘብ መሆኑን እንረዳለን። (ራእ፫÷፯፣ ፩÷፱)

በዘመነ አሪት እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ ሞአባውያንና አሞናውያን እንጀራና ውኃ ይዘው አልተቀበሏቸውም። በእርግማንም እንዲጠፉ በለዓምን አምጥተውና ዋጋ ሰጥተው ሊያስረግሟቸው ሞክረዋል፤ በዚህ ምክንያት ሞአባውያንና አሞናውያን እስከ አሥር ትውልድ ድረስ ወደ ቤተ መቅደስ እንዳይገቡ እግዚአብሔር አውግዟቸዋል። የአሪት ካህናትም ይህንን የእግዚአብሔር ውግዘት በተጠንቀቅ ያስፈጽሙ ነበር። (ዘዳ፳፫÷፬-፰) እንዳይገቡ መከልከል ማውገዝ ነው። ይህ ደግሞ ለፈጣሪ የባሕርይ ገንዘቡ ነው።

የማውገዝ ሥልጣን ለካህናት በጸጋ ስለመሰጠቱ

ማውገዝ የፈጣሪ የባሕርይ ገንዘብ ነው። ‹‹ጠንዘቡ የወደደውን ለማድረግ›› ሥልጣን አለውና በቸርነቱ ይህንን ሥልጣን ለካህናት በጸጋ ሰጣቸው። (ማቴ፳÷፲፭) ‹‹**በዘአእመረ መንፈስ ቅዱስ**›› እንዲሉ ‹‹እርሱ መንፈስ ቅዱስ ባወቀው›› ይህን ‹‹ታላቅ›› ሥልጣን ለካህናት የሰጣቸው ሕገ ወጥ የሆኑ ሰዎች ምእመናንን እንዳያናውጧቸው ለምእመናን ድኅነትና ዕረፍት አስቦ ነው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ›› በማለት በተናገረው ቃል መሠረት እግዚአብሔር ከባሕርይ ገንዘቦቹ ብዙ ነገር ለሰው ልጆች በጸጋ ሰጥቷል። (፪ጴጥ፩÷፬) ይህም ገቢረ ተአምራት ወመንክራትን፣ ሀብተ ፈውስንና የመሳሰሉት ሁሉ ይጨምራል። ይህም ድንቅ አይደለም። ለካህናት ‹‹**የማይፈታውን ይፈቱ ዘንድ**›› ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ‹‹ምጡቅ›› ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል። ማውገዝ መቻልም የዚህ ስጦታ አንዱ ክፍል ነው።

ቀደም ሲል እንደተብራራው ‹‹እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ›› የሚለው ቃል ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን መቀበላቸውን የሚያሳይ ነው። (ማቴ፲፱÷፳፰) እንደዚሁም አምላካችን ለቅዱስ ጴጥሮስና በእርሱም በኩል ለሁሉም ሐዋርያት በአንድነት የማሰርና የመፍታትን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። (ማቴ፲፮÷፲፰-፲፱፣ ፲፰÷፲፰-፲፱)

ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን የተቀበሉት ጌታችን እፍ ብሎባቸው «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸውም ተይዘባቸዋል» ባላቸው ጊዜ ነው። (ዮሐ፳÷፳፪) ይህ የክህነት ሥልጣን በሐዋርያት ብቻ ተወስኖ አልቀረም። እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ የሚነሡና ብቁ ሆነው የሚገኙ ሁሉ ይህን ሥልጣን ሊቀበሉ ይችላሉ። ይህም «እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» በማለት በተናገረው የአምላካችን ቃል ታውቆአል። (ማቴ፳፰÷፳) ምክንያቱም

www.zeyeneta.com

ሁሉም ሐዋርያት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በሕይወተ ሥጋ አልኖሩምና፡፡ ይህ ቃል በእግረ ሐዋርያት ተተክተው የእነርሱን አሰረ ፍኖት ተከትለው ለሚነሡ ካህናት ሁሉ የተነገረ ቃል ኪዳን ነው፡፡

በተያያዥም ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታ የሰጣቸውን የክህነት ሥልጣን ለሊቃውንት ማስተላለፋቸውን ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ሲል ያስረዳል፡፡ «ከመለኮትህ ገናንነት ምሥጢር ለደቀ መዛሙርትህ እንዳልሰወርህ እነርሱም ከእኛ የሰወሩት የለም፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሊቀ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት አድርገው ሾሙን እንጂ፡፡» (ቅዳሴ አትናቴዎስ ቁ፩)

ክህነት ከፈጣሪ የተገኘ ስለሆነ ካህናት አጥፊን ለመለየት ሲያወግዙ ከፈጣሪ ፈቃድ ጋር መስማማታቸውን ያሳያሉ፡፡ የካህናት ማውገዝ የፈጣሪን ፈቃድ በግልጽ ማጽደቅና ማሳየት ነው እንጂ ፈጣሪን መቅደም ወይም ፈቃዱን መጻረር አይደለም፡፡

ቅዱስ ወንጌል ‹‹በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል›› ቢልም እነርሱ ያወገዙትን ሁሉ አግባብነት ባይኖረውም ፈጣሪ በሰማይ ያሰረዋል ማለት አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው ከካህናት ውግዘት የሚቀድመውም የፈጣሪ የራሱ ውግዘትና እርግማን ነው፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ንባብና መንፈስ ስምምነት በሌለው መንገድ የሚደረግ ውግዘት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውምና አያስኮንንም፡፡

ምዕራፍ ሦስት

ሥልጣነ ክህነት ከውግዘት አንጻር

በኦሪትና በአዲስ ኪዳን

ማውገዝ ወይም ከውግዘት መፍታት በዘመነ አዲስ በሐዋርያት የተጀመረ እንግዳ ነገር ሳይሆን በዘመነ ኦሪትም በሌዋውያን ካህናት ዘንድ ይሠራበት የነበረ እጅግ የታወቀ ሥርዓት ነበር፡፡ ምክንያቱም የቤተ መቅደስ ካህናት በብሉይ ኪዳን ዘመን ይህን መሰል ሥልጣን ነበራቸው፡፡ የብሉይ ኪዳን ካህናት በአንብሮተ እድ በተሾሙ ጊዜ አንድ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰውን እንደ ጥፋቱ ዓይነት አይተውና ለይተው ወደ ቤተ መቅደስ እንዲገባ ለመፍቀድ፣ እንዳይገባም ለመከልከል ሥልጣንን ተቀብለዋል፡፡

አንድ ሰው ወደ ቤተ መቅደስ እንደይገባ ‹‹መከልከል›› እንደ ‹‹ማሰር›› ሲሆን እንዲገባ ‹‹መፍቀድ›› ደግሞ እንደ ‹‹መፍታት›› ይቆጠራል፡፡ አይሁድ ይህንን ሥልጣን እስከ ዘመነ ወንጌል ድረስ ሲሠሩበት ተገኝተዋል፡፡ ለዚህም ማስረጃው በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንንና ስለ እርሱም መመስከርን እንደ ከባድ ወንጀል (ኃጢአት) በመቁጠር በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነና ስለእርሱም የመሰከረ ‹‹ከምኩራብ እንዲሰደድ›› በአንድ ልብ ሆነው አውግዘው ነበር፡፡ (ዮሐ፱÷፳፪፣ ፲፪÷፵፪)

ኦሪት ለወንጌል መርገፍ ወይም ጥላ የሆነችውን ያህል የኦሪትም ካህናት ለወንጌል ካህናት ምሳሌና ጥላ ነበሩ፡፡ ከኦሪት

www.zeyeneta.com

ካህናት የወንጌል ካህናት በሁሉም አቅጣጫ ይከብራሉ። ወንጌል ከኦሪት የምትለየውንና የምትበልጠውን ያህል ደግሞ ካህናተ ወንጌል ከካህናተ ኦሪት የተለዩና የበለጡ ናቸው። የዘመነ ኦሪት ክህነት ምሳሌ ከመሆን የማያልፍና ጥቅሙ በምድር ላይ ብቻ የተወሰነ ነበር። የዘመነ ወንጌል ክህነት ግን ምሥጢሩና ጥቅሙ እስከ ሰማይ ዘልቋል። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል›› ብሏልና። (ማቴ፲፮፥፲፱)

«ዘወሀብክነ ... ከመ ንፍታሕ ዘኢይትፈታሕ» ወይም በአማርኛው ‹‹የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ የሰጠኸን» የሚለውን የጸሎተ ኪዳን ኃይለ ቃል መምህራን ሲተረጉሙ «ሌዋውያን ካህናት አያስቲሥርዩት የነበረውን ውሳጣዊ ኃጢአት እናስተሠርይ ዘንድ የሰጠኸን» ማለታቸው የሐዲስ ኪዳን ክህነት ከቀደመው መብለጡን ያሳያል።

ካህናት የሚያወግዙትን ሰውና ድርጊቱን አስቀድመው በፈጣሪ ዘንድ መወገዙን ማወቅ ይገባቸዋል። ይህም ማለት ያ ተግባር በቅዱስ መጽሐፍ ሚዛንነት ሲታይ ‹‹የተወገዘ ነው? ወይስ አይደለም?›› ብለው መጠየቅ አለባቸው። በአጭሩ ከማውገዝ በፊት አንድን ድርጊት የሚያስወግዝ መሆንና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል። የእነርሱ ውግዘት መካሄድ ያለበት ከዚህ በኋላ ነው። ይህን ካደረጉ ከፈጣሪ ፈቃድ ጋር ተስማምተዋልና እነርሱ በምድር ያሰሩትን ፈጣሪ ደግሞ በሰማይ ያስረዋል። ያወገዙትንም ያወግዘዋል።

ምዕራፍ አራት

ውግዘት የሚያስከትለው ጉዳት

ኃጢአትና ክህደት ጉዳት ሳያስከትሉ አይቀሩም። በዘመነ ኦሪት ኃጢአት ወዲያውኑ ቅጣት ያስከትል ነበር። በዘመነ ሐዋርያትም ቢሆን ይህ የታየበት ጊዜ አለ። ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ ቅዱስን ሊያታልሉ ልባቸው በደፈረ ጊዜ በቅዱስ ጴጥሮስ ተገሥጸዋል። በዚህ ጊዜ ባልና ሚስቱ ሐናንያና ሰጲራ በሥጋቸው ተቀሥፈዋል። በአንድ ዕለት ሞተው በሦስት ሰዓታት ልዩነት በየተራ ተቀብረዋል። (የሐዋ፭፥፩-፲፩)

ቅዱስ ጳውሎስም ሳይገባቸው ቅዱስ ቁርባንን የተቀበሉ ሰዎች ምን እንደደረሰባቸው ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል፡ ‹‹ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ። አያሌዎችም አንቀላፍተዋል።›› (፩ቆሮ፲፩፥፴) ‹‹መታመም›› በሥጋ ደዌ መሰቃየት አይደለምን? ‹‹አያሌዎችም አንቀላፍተዋል›› ሲል ደግሞ ሞተዋል ማለቱ እንደሆነ ግልጥ ነው።

በኃጢአቱ ምክንያት በሥጋም በነፍስም የሚቀጣ ሰው አለ። በሥጋ ተምሮ በነፍሱ የሚቀጣ ሰው አለ። ለምሳሌ፦ እንደ ነዌ። ነዌ በዚህች ምድር በቅንጦት የኖረና በሰማይ የተሰቃየ ሰው ነው። (ሉቃ፲፮፥፲፱-፴፩) በሥጋ ተቀሥፎ በነፍስ ግን ምሕረት የሚያገኝ ሰው ደግሞ አለ። ይህም እንደ ኃጢአቱ ክብደትና ቅለት ነው። ይሁዳ በነፍስና በሥጋው ተጎድቷል። ሐናንያና ሰጲራ ደግሞ በሥጋ

www.zeyeneta.com

ተቀሥፈው በነፍስ ተምረዋል። (የሐዋ ፭፥፩-፲፩ ትርጓሜ) ቁስለኛው አልዓዛርም በምድር (በሥጋ) ተጎድተው በሰማይ ለጸደቁት እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል ነው። (ሉቃ ፲፮፥፲፱-፴፩፣)

ውግዘት መንፈሳዊ ቅጣት እንደ መሆኑ መጠን በሥጋ ቅሥፈት በነፍስ ደግሞ ፍርድን ማምጣቱ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ውግዘት ፍትሐ እግዚአብሔር እንደመሆኑ መጠን የሚያስከትለው ውጤቱ ሊመረመር አይቻልም። አንድ ሰው ተወግዞ ሳለ በውጭ የሚታይ ምንም ዓይነት ቁሳዊ፣ አካላዊና መንፈሳዊ ጉዳት ካልደረሰበት ውግዘቱ አልሠራም ወይም ያ ሰው የተወገዘው ያለአግባብ ነው ለማለት አያስደፍርም።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለሌሎች ግልጽ ባልሆነ ነገር ግን ተቀጪው ሰው ብቻ ሊረዳው በሚችለው መንገድ ሊቀጣ ይችላል። ይህንንም ሊያደርግ የራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ለምሳሌ ሊቀ ነቢያት ሙሴን በማማት ካህኑ አሮንና እኅቱ ማርያም በአንድነት ተባብረዋል። ነገር ግን በለምጽ ስትቀጣ የምናየው ማርያምን ብቻ ነው። ይህም የሆነው አሮን ካህን በመሆኑ ለምጽ ቢወጣበት እንደ ዘመኑ ሕግ ለክህነት ስለማይበቃና በተጨማሪም ምንም ቢያጠፉ ካህናትን ማክበር እንደሚገባ ለማስተማር አሮን በግልጽ አልተቀጣም። (ዘኁ ፲፪፥፩-፲፭ ትርጓሜውን ተመልከት) ይህም ሲባል እንደ ማርያም በለምጽ አይሁን እንጂ ካህኑ አሮን ያለ ቅጣት እንዳልቀረ ማስተዋል ይገባል። እግዚአብሔር በረቂቅ የሚቀጣበት

ጊዜ አለ። በግልጽ የሚቀጣበትም ጊዜ አለ። ኃጢአቱ የሚቀድመው ሰው አለ ኃጢአቱ የሚከተለውም ሰው አለ።

ውግዘት የሚያስከትለው ጉዳት እንደ በደሉ ዓይነት የተለያየ ነው። ከምእመናን መለየት፣ በሥጋ ተቀሥፎ መሰቃየት፣ ጠና ካለም ወዲያው መሞት ይኖራል። ይህም ‹‹ሞተ ቅሥፈት›› ይባላል። ከውግዘት በኋላ የተከሠተ ሞተ ቅሥፈትና ይህን የመሰለ ጉዳት ሁሉ የውግዘት ውጤት ተደርጎ ይቆጠራል። ቀደም ሲል እንደተብራራው ውግዘት ፍትሐ እግዚአብሔር ነውና።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል የአባቱን ሚስት ያገባውን ሰው ‹‹ይህን የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ›› በማለት አውግዞታል። ቀጠል አድርጎም ‹‹እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው›› በማለት ውግዘቱን አጠናክሮታል። (፩ቆሮ ፭፥፫፣ ፭፥፭)

ሐዋርያው ያስተላለፈው የውግዘት ቃል ውግዘት የሚያስከትለውንም ጉዳት ጨምሮ ያሳያል። መወገዝ ለሰይጣን መሰጠት ነው። ምክንያቱም ውግዘት ሐዋርያው እንደተናገረው ‹‹ከመካከል መወገድ›› ወይም ከቤተ ክርስቲያን መለየት ስለሆነ ለሰይጣን እንደመሰጠት ነው። በዚህ ሥጋዊ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የደኅንነት ክልል ናት። ከቤተ ክርስቲያን ክልል ውጭ ያለው እድሞ ደግሞ እንደ ሰይጣን ግዛት ይቆጠራል። (ሉቃ ፬፥፮፣ የሐዋ ፳፮፥፲፰፣ ቆላ ፩፥፲፫፣ ፩ዮሐ ፭፥፲፱)

www.zeyeneta.com

‹‹ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዱ ነው›› ሲል ሁለት ነገሮችን ያሳያል። አንደኛው ‹‹ለሥጋው ጥፋት›› ሲል ‹‹ሥጋዊነቱ እንዲጠፋ›› ማለትም ሥጋዊ ምኞቱ እንዲጠፋ ከቤተ ክርስቲያን ይለዩት ማለት ነው። ይህም የት እንደወደቀ አስቦ ከንዘንና ከአፍረት ብዛት ከብቸኝነቱም ስሜት የተነሣ ‹‹ዐሠራው ኃጢአት እንዲጸጸትና ከሥጋዊ ምኞቱ ሽሽቶ ከጥፋት እንዲድን ለማድረግ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ ቀደም ሲል እንደተብራራው ሰው ኃጢአት ሲሠራ ሲወገዝ በሥጋው ይቀሠፍ ነበርና ሐዋርያው ‹‹ለሥጋው ጥፋት›› ያለው ይኸንን ይዞ ነው። መወገዝ ለሰይጣን መሰጠት እስከሆነ ድረስ ሰይጣን በሥጋ ላይ ልዩ ልዩ ደዌ ለማምጣት መቻሉም ይታወቃል። (ሉቃ፲፫፥፲፮፣ ፪ቆሮ፲፪፥፯) ስለዚህ የተወገዘ ሰው የሰይጣን መጫወቻ ይሆናል። መቅሠፍትና ደዌ ሥጋም አያጣውም።

ቅዱስ ዳዊት ‹‹*ሞቱ ለኃጥእ ጸዋግ*›› ማለትም ‹‹የኃጥእ ሰው ሞት ክፉ ነው።›› (መዝ፴፫፥፳፩) እንዳለ አርዮስ ቦኑባኤ ኒቂያ በደረሰበት ውግዘት ምክንያት ክፉ አሟሟት ሞቷል። አሟሟቱ በቁስጥንጥንያ መካነ ምኩሳሕ ወይም ዐጸደ ምኩሳሕ (የሕዝብ መጸዳጃ ቦታ) የሆድ ዕቃው (ንዋየ ውስጡ) ተዘርግፎ ነው። ይህ የአርዮስ የመቅሠፍት አሟሟት የውግዘትን ኃይል ያሳያል። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፻፳)

ንስጥሮስን ጨምሮ ሌሎችም የተወገዙ ሰዎች አሟሟታቸው ክፉ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዱናል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በግፍ ሥራዋ ያወገዛት ንግሥት አውዶክስያ ተዘልላ አልተቀመጠችም። ‹‹*ወአመንደባ በደዌ ዓቢይ*›› እንዲል በጽኑ ደዌ ተመትታ ብዙ ተሰቃይታለች። የምትድን መስሏት ለሕክምና ብዙ ገንዘብ ብታፈስም ባሰባት እንጂ አልተሻላትም። በዚህ ምክንያት ‹‹*ወአልቦ ዘበቁዓ ዘእንበለ ዘአልሐማ*›› ተብሎ ስለእርሷ ተጽፏል። ‹‹ሕክምናዋ አባሰባት እንጂ የጠቀማት የለም›› እንደማለት ነው። በመጨረሻ መካሪ አግኝታ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መቃብር ሄዳ ወድቃ ተነሥታ በመማጸኗ ፈጣሪ ይቅር ብሏት ተፈውሳለች። (ድር ዘዮሐ አፈ የታሪክ ዓምድ)

‹‹ከአንድ መቶ አመት በፊት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. በትግራይ ክፍለ ሀገር አዝላ በምትባል ሥፍራ ሠራዊታቸውን ይዘው በመጡ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን የዘረፈ ወታደር ሁሉ ንዋያተ ቅድሳትን እንዲመልስ አዋጅ አስነገሩ። ካህናትም መልሱ ብለው አዘዙ፤ የማይመልሰውንም አወገዙ። ይሁንና ከንጉሡ ወታደሮች መካከል የነበረ አረማዊ ወታደር ከመቅደስ የዘረፈውን መስቀል ላለመመለስ ወደ ኮራብ ሸሸ።

ይህም ነገር ከአጼ ምኒልክ ጆሮ ደረሰ። ንጉሡም ወደ እመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በመሄድ «እመቤቴ ሆይ የዚህን የሰነፍ ጭፍራ ያደረገውን መገዳደርና በልጅሽ መስቀል ላይ የፈጸመውን ድፍረት እንዲሁም በሰማይና በምድር ያስሩና ይፈቱ ዘንድ ሥልጣን በሰጣቸው በካህናት

www.zeyeneta.com

ላይ ያደረገውን ተሳልቆና ዝብብት ተመልከች» በማለት ጸለዩ። ከዚህ በኋላ ይህ አረማዊ በደዌ ተያዘ በሕልምም ይጨነቅ ጀመር። በዚህን ጊዜ መስቀሉን መለሰ መስቀሉም አባ ኃይለ ሥላሴ በሚባሉ ተንቤን በሚገኙ መነኩሴ እጅ ወደ አብርሃ ወአጽብሐ ቤተ ክርስቲያን ተልኳል።››

ይህ ታሪክ ግዝት በነፍስና በሥጋ የሚያስፈርድ ፍልመሆኑ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው በማለት ክብረ ክህነት መጽሐፍ ተአምረ ማርያምን ጠቅሶ ይተርካል። (ክብረ ክህነት ገጽ፷፮፣ ተአ.ማር. ፫፻፵፮)

ይህ ሁሉ ሆኖ የተወገዘው ሰው ንስሐ ካልገባና ካልተመለሰ ከሥጋ መቀጣቱ ብቻ ከበደል ነጻ አያደርገውም። በመጨረሻ ለማያዊ ፍርድ ያገኘዋል። ከውግዘቱ ያልተፈታ እርጉም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባምና። የእግዚአብሔር መንግሥት ‹‹የአባቴ ቡሩካን›› ለተባሉ እንጂ ለውጉዛን አይደለችምና።

አንዳንዶች ውግዘት ከመንግሥተ ሰማያት አይለይም ይላሉ። ውግዘት ሥርዓት እንጂ የጽድቅና የኩነኔ ጉዳይ አይደለም ማለት ከባድ ጥፋት ነው። ‹‹በምድር ያሰራችሁት በሰማይም የታሰረ ይሆናል።›› የሚለው የጌታችን ቃል የሚታበል አይደለምና። የተወገዘ ሰው ሳይመለስና ከውግዘቱ ሳይፈታ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ ከሆነ ‹‹በሰማይ የታሰረ ይሆናል›› መባሉ ከንቱ ነዋ? አትሳቱ! እግዚአብሔር እንደ ሰው አይዋሽም። በተገቢ ሁኔታ የተወገዘ ሰው ተጸጽቶ ሳይመለስና ከውግዘቱ ሳይፈታ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም።

ምዕራፍ አምስት

ከማውገዝ በፊት ስለመታገሥ

ግዝት ማለት አንድ ምእመን ከሃይማኖት ወጥቶ ከምግባር አድጦ ሲገኝና ተመክሮ አልመለሰም ሲል ከሕዝበ ክርስቲያን እንዲለይ በሥልጣነ ክህነት የሚፈጸም መንፈሳዊ ቅጣት ነው። ስለዚህ ደርሶ ማውገዝና መገዘት አይገባም። ምክንያቱም ግዝት ሰውን ከእግዚአብሔር አንድነት ለይቶ እስከ ለሌለው ዘመናት ከመንግሥተ ሰማይ የሚያርቀው ስለሆነ ነው። ማውገዝ ወደ ገሃነም የሚያወርድ ፍርድ በመሆኑ በችኮላ መደረግ የለበትም። ያለ በቂ ትዕግሥት በሰው ላይ ይህን ያህል ጭካኔ ማድረግ አይገባምና።

ከማውገዝ አስቀድሞ በትዕግሥት መላልሶ ማስተማር፣ ሳይታክቱ መምከር፣ እምቢ ያለ እንደሆነ መገሠጽ ያስፈልጋል። ከዚህ በኋላም እንደ ጥፋቱ ዓይነት እያዩ በመታገሥ በቂ ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው። ፈጣሪ ለሰው አዛኝ፣ ርኅሩኅና መሐሪ ስለሆነ ከሰዎች መካከል አንድም እንኳን እንዲጠፋበት አይፈልግም። (ማቴ፲፰፥፲፪-፲፬፣ ሉቃ፲፭፥፫-፯፣ ሕዝ፲፰፥፳፫) ካህናትም የእርሱ እንደራሴ እንደመሆናቸው መጠን እንዲሁ መሆን አለባቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው። ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር

www.zeyeneta.com

ውሰድ። እነርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት።›› ይላል። ይህ ቃል የበደለን ሰው ገዝቶ ከመለየት በፊት ምን ማድረግ እንደሚገባ አስተማሪ ነው። ከዚህም በመነሣት ከማውገዝ በፊት መታገሥና መላልሶ ማስተማር የወንጌል ትምህርት ብቻ ሳይሆን ሥርዓትም ጭምር መሆኑን መረዳት ይቻላል። ቤተ ክርስቲያን ለሺህ ዓመታት በዚህ መንገድ ተጉዛለች።

በተደጋጋሚ ተመክሮና ተገሥጾ አልሰማ ያለ ሰው ይወገዛል። ‹‹ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።›› ይላልና። ተጸጽቶ ከጥፋቱ ቢመለስ ግን ሰባቱን አንድ እያሉ እስክ ሰባ ጊዜ ያህል ይቅርታ ሊያድርጉለት ይገባል። ይህም ቃል ቢያለኛን ሰው ምን ያህል መታገሥ እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። (ማቴ፲፰÷፲፭-፲፯፤ ፲፰÷፳፩-፳፪)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የካህን ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት መስፈርት ሲያስቀምጥ ‹‹*ዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ*›› ብሏል። ይህም ‹‹ካህን ለመማታትና ለመገዘት ፈጥኖ እጁን የማያነሣ›› ሊሆን ይገባዋል ማለት ነው። (፩ጢሞ፫÷፫ ትርጓሜን ተመልከት) መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ሁሉ ‹‹ለቁጣ የዘገየ›› ይሁን ካለ ካህናት ለማውገዝ ምን ያህል መታገሥ ይገባቸው ይሆን? (ያዕ፩÷፳)

አውዶክስያ የተባለች ንግሥት የድሀ መሬት በግፍ በቀማች ጊዜ የ‹‹ድሆች ጠበቃ›› የተሰኘው ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አውግዟታል። ነገር ግን ይህን ያደረገው ድንገት ደርሶ ሳይሆን

ከተበዳይዋ ደሀ ጋር ለማግባባትና ለመገላገል አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ካደረገ በኋላ ነበር።

በኋላም ፤ሴቲቱ ከግዝት እንዲፈታት ቴዎፍሎስና ኤጲፋንዮስ የተባሉ ጳጳሳትን ልካበታለች። የተላኩትም ወደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ መጥተው አንድ ሰው ሲያጠፋ ጥፋቱ ‹‹የሃይማኖት እንደሆነ ዕለቱን ጠንክር ይሉበታል። የምግባር ከሆነ ግን እያደር ይሆናልና ይህችን ሴት ከግዝት ፍታት›› አሉት። (ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የታሪክ ዓምድ)

እዚህ ላይ የተጠቀሱት ጳጳሳት ‹‹የሴቲቱ ጥፋት የምግባር ነውና ልትገዘት አይገባም›› አለማለታቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ነገር ግን የጥፋቷን ዓይነት በመለየት እንዲታገሣት ማልደዉታል። ከዚህ ታሪክ የምንማረው ከውግዘት በፊት የጥፋቱን ዓይነትና መጠን በመመርመር ተገቢውን ትዕግሥት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ነው።

ቅዱስ ወንጌል እንደሚነግረን በወልድ ያላመነ ‹‹በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።›› (ዮሐ፫÷፲፰) ይህ ፍርድ ዕለተ ኩነኔን ወይም ዕለተ ምጽአትን አይጠብቅም። ቃሉ የሚለው *‹‹ወድአ ተኰነነ››* ማለትም ‹‹አሁን ተፈርዶበታል›› ነውና።

በወልድ ያመነ ግን ሥራው ተመርምሮ ፍርድ ለማግኘት ዕለተ ሞቱን ወይም ዕለተ ምጽአትን ይጠብቃል። ይህ ፈጣሪ ለሰው ልጆች የወሰነው የፍርድ ሂደት ምን ያሳያል? ካህናት የምግባር

www.zeyeneta.com

ችግር ያለበትን ሰው በትዕግሥት ሊጠባበቁት የሃይማኖት ችግር ያለበትን ሰው ግን በቶሎ እርምጃ ሊወስዱበት እንደሚገባ አያሳይምን? ቀደም ሲል እንደተብራራው ውግዘት ፍርድ ነውና።

ቅዱሳን አባቶች ጥፋተኛን ሰው አውግዘው ከመለየታቸው በፊት ፍጹም ትዕግሥት ያሳዩ ነበር። ትዕግሥታቸው አግባብ የሌለው እስከመስል ድረስ ይታገሡ ነበር። ለምሳሌ፡- ሠለስቱ ምእት በአርዮስ ምክንያት በኒቂያ በተሰበሰቡ ጊዜ ምልአተ ጉባኤ ሲሆን አርዮስን ከማነጋገርና ከማውገዛቸው በፊት ከመሸከረም ሃያ አንድ እስከ ጎዳር ዘጠኝ ሱባኤ ገብተዋል።

የሲሜን ሽዋ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አባ ጎርጎርዮስ ይህንን ታሪክ ሲመዘግቡ ‹‹ጠላትን አስቀምጦ አርባ ቀን ሙሉ ሱባኤ መግባት አመች መስሎ ባይታይም ወዲያው ተሰብስበው መሟገት ጀመሩ ከማለት ሱባኤ ገብተው ነገሩን አመለከቱ ማለቱ ነገሩ የበለጠ መንፈሳዊ መሆኑን ያሳያል።›› በማለት የቅዱሳን አበውን ትዕግሥትና መንፈሳዊነት አድንቀው አልፈዋል። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ምዕ፯)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጥፋተኛን አውግዞ ከመለየት በፊት ምን ያህል መታገሥ እንደሚገባ በሕይወቱ ሰብኳል። ከዚህም በተጨማሪ አጥፊዎችን በውግዘት ከማስፈራራት ይልቅ በፍቅር መሳብ የበለጠ መሆኑን ሲያስረዳ ‹‹*ወባሕቱ ኢንትቤቀል እምኔክሙ። ወኢንመልሕ ሰይፈ በላዕሌክሙ። አላ ናስተሐምም*

ለመድኃኒትክሙ።›› ብሏል። ይህም ‹‹ቂም እንይዝባችሁም፤ በእናንተ ላይ ሰይፋችንን አንመዝም (አናወግዛችሁም) ድኅነት ታገኙ ዘንድ እንተጋላችኋለን እንጂ›› ማለት ነው። በችኮላ ማውገዝ ፈጥኖ ሰይፍን በሰው ላይ እንደመምዘዝ ይቆጠራል። ይህ ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስን እንዳስገሠጸው ያስገሥጻል እንጂ ጤናማ አካሄድ አይደለም። (ተግ ዘሮሐ አፈ፬፤ ማቴ፳፮÷፶፩-፶፪)

ተጣድፎ ከማውገዝ አጥፊዎቹ ግለሰቦች የሚመለሱበትን መንገድ ሳይታክቱ ማፈላለግ ቅድሚያ የሚሰጠው መንፈሳዊ ሥራ ነው። ሳኦል በተደጋጋሚ ፈጣሪን ቢበድልም ቀብቶ ያነገሠው ነቢዩ ሳሙኤል ከፍተኛ ትዕግሥት አሳይቷል። ከዚህም በላይ ቀን ከሌሊት ከፅንባ ጋር ምሕረት እንዲያገኝ ወደ ፈጣሪ ይለምንለት ነበር። ይህንንም እግዚአብሔር ራሱ ‹‹በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው?›› እስኪለው ድረስ መደበኛ ሥራው አድርጎት ነበር። ይህን ታሪክ በሚገባ ላስተዋለው እንኳን ለመንጋ እረኞች ለካህናት ይቅርና ለምእመናንንም እጅግ ብዙ ነገር ያስተምራል። (1ሳሙ06÷1)

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ስድስት

‹‹ከንቱ ግዝት››

ያለ አግባብ የሚደረግ ግዝት አይሠራም። ገዛቹም ‹‹ወፈ ገዝት›› ይባላል። ይሁን እንጂ ፍትሐ እግዚአብሔር አይታወቅምና ምንም ጊዜ ቢሆን የተገዘተ ሰው አውጋዡን ‹‹ወፈ ገዝት›› ብሎ ነገሩን ከሚንቅ ቃለ ካህንን አክብሮና ፈርቶ ይቅርታ ቢጠይቅ መልካም ነው። ሐና እመ ሳሙኤል (የሳሙኤል እናት)ም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት። ካህኑ ዔሊ ባላወቀው ነገር በድፍረት ቢናገራትም በትሕትና መልሳለታለች እንጂ ጥፋት ስለሠራ ብላ የድፍረት ቃል አልመለሰችለትም። (፩ሳሙ፩÷፲፪-፲፰)

አንድ ሰው ጥፋት ያልሠራ ቢመስለውም እንኳን ቃለ ካህንን አክብሮ ይቅርታ መጠየቁ ደፋር ከመሆን ያድነዋል። የትሕትናንም ልብስ ያጎናጽፈዋል። በዚህ ትሕትናው ምናልባት ግዝቱ ባልታሰበ ረቂቅ መንገድ አግባብነት ያለው ሆኖ ቢገኝ ከመኮነን ያመልጣል። አውጋዡ ሰው ካህን መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ግዝትን መናቅ በምንም መንገድ ቢሆን መንፈሳዊነት ሊሆን አይችልም። ልበ አምላክ የተሰኘ ቅዱስ ዳዊትም ምንም ወንጀለኛና ኃጢአተኛ ሆኖ ቢያገኘውም ‹‹እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን አላነሣም›› አለ እንጂ ሳኦልን አልተዳፈረም። (፩ሳሙ፳፬÷፮)

ካህናት እርሱ በሰጣቸው ሥልጣን ከፈጣሪ ፈቃድ በወጣ መንገድ ማውገዝ አይችሉም፣ አይገባቸውምም። የካህናት ውግዘት

ተቀባይነት የሚኖረው ውግዘቱ የመጽሐፍ ቅዱስን ዓላማና ሐሳብ የተከተለ ከሆነ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን በራሳቸው ላይ እርግማንን ሊያመጣ ይችላል። ሐዋርያው እንዳስተማረው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየን ነገር የሚያደርግ ሁሉ ‹‹ማንም ቢሆን የተረገመ›› ይሆናልና። ሐዋርያው ‹‹ማንም ቢሆን›› ሲል ቄስም፣ ጳጳስም ቢሆን ማለቱ ብቻ አይደለም። ከዚህም በላይ ከፍ ብሎ የ‹‹ሰማይ መልአክም›› ቢሆን ብሏል። ስለዚህ ‹‹ማንም ቢሆን›› ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ ነገር ማድረግ አይችልም። ይህ ማስጠንቀቂያ ደግሞ ከንቱ ውግዘትንም ይጨምራል። (ገላ፩÷፰-፱)

አግባብነት በሌለው ውግዘት ፈጣሪው ባልጨከነበት ፍጡር ላይ ጠፍቶ እንዲቀር መጨከን ታላቅ በደል ነው። የማይገባ ግዝት ቢሞከርም በፈጣሪና በሰው ዘንድ ትዝብት ላይ ይጥላል እንጂ ተወጋዡን አይጎዳም። ቅባት የተዋሐደውን ጨርቅ ውኃ እንደማያርሰው ሁሉ ቅብዓ መንፈስ ቅዱስ ያልተለየውን ቅዱስ ሰውም ቢወገዝ እርግማን አያድርበትም።

አግባብነት የሌለው ግዝት እንደማይጎዳ ማስረጃው በመጽሐፈ ምሳሌ የሰፈረው ቃል ነው። ቃሉም ***‹‹በከመ አዕዋፍ ሠራርያት ወከመ እብን ዘይወግሩ ላዕለ ከማሁ መርገም ዘበከንቱ ኢይበጽሕ ኀበ መኑሂ››*** ይላል። በአማርኛ ‹‹ወፎች በረው በረው ከዛፍ፣ ጦር ተወርውሮ ድንጋይ ተጥሎ ከመሬት ሳያርፉ እንደማይቀሩ እንደዚሁ በማይገባ የሚደረጉ እርግማንና ውግዘትም ተመልሰው ረጋሚውንና

www.zeyeneta.com

ገዛቹን ይጎዳሉ እንጂ ተረጋሚውንና ተገዛቹን አይጎዱትም።›› ማለት ነው። (ምሳ፳፮፥፪ ትርጓሜውን ተመልከት)

አንድ ሰው ያለ አግባብ ከተወገዘ እግዚአብሔር ይቀበለዋል እንጂ ፈጣሪ እንደ ሰው ተደምሮ አያወግዘውም። ይህንንም ሲያስረዳ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አይሁድ ከምኩራባቸው አስወጥተው እንዳባረሩት ጌታችን አውቆ ከደጅ ተገናኝቶታል። ቀጥሎም ‹‹አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?›› በማለት ጠየቀው። ያም ሰው መልሶ ‹‹ጌታ ሆይ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ። ኢየሱስም፦ አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው። (ዮሐ፱፥፴፭-፴፯) እርሱም ጌታ ሆይ አምናለሁ አለ ሰገደለትም።›› ይላል። አምላካችን ይህን ማድረጉ በግፍ ወይም ያለ አግባብ ከምእመናን ቢለዩአችሁ፣ ከቤተ ክርስቲያን ቢያባርሯችሁና ቢያወግሟችሁ እኔ እቀበላችኋለሁ ማለቱ እንደ ሆነ ይታወቃል።

አይሁድ ከምኩራብ ለይተው ማባረራቸው እንደዘመናቸው ማውገዛቸው እንደነበር ቀደም ሲል ተብራርቷል። እዚህ ላይ ሌላም ልብ ሊሉት የሚገባ ጉዳይ አለ። እርሱም ይህ ዓይነ ስውር የነበረ ሰው ምንም እንኳን አይሁድ በክርስቶስ ያመነ ከምኩራብ እንዲሰደድ አስቀድመው አውግዘው የነበረ ቢሆንም የውግዘት ቃላቸውን በመስማት ብቻ ከምኩራብ አልወጣም። ምክንያቱም ግዘታቸው አግባብ ስላልነበረ ነው። በመጨረሻ ግን እያዳፉ በጉልበት አስወጥተውታል። ስለዚህ ፍቅረ ቤተ ክርስቲያን በልቡ ያለ ሰው

‹‹በሐሰት ተወገዝኩኝ›› እያለ በምሬት በገዛ ፈቃዱ ከቤተ ክርስቲያን አይርቅም። ይህን የሚያደርግ ካለ አስቀድሞም ልቡ ከቤተ ክርስቲያን አለመኖሩን ያሳያል።

ከንቱ ግዝት ወደ ራስ ስለመመለሱ

ያለአግባብ የሚደረግ ግዝት ‹‹አይደርስም፣ ከንቱ ግዝት ነው።›› ተብሎ ብቻ የሚያበቃ ነገር አይደለም። በተገዛቹ አይድረስ እንጂ ገዛቹን ሳይጎዳው አይቀርም። ያለ አግባብ የሚያወግዝ ካህን ራሱ ውጉዝ መሆኑ ከመገዘቱ በፊት በጉዳዩ እንዲያስብበትና እንዲታገሥ ያደርገዋል። ይህ ዓይነቱ ስጋት ካህናት የማሰር ወይም የመገዘት ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ እንዳይጠቀሙ ይይዛቸዋል።

ያለ አግባብ ማውገዝ ራስን ማውገዝ እንደሆነ ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ እንዲህ ይላል። ***‹‹ሊይሰዓር ወሊያውግዝ ዘእንበለ ርትዕ ወለእመ አሰረ ወአውገዘ ዘእንበለ ርትዕ ውእቱኒ ይከውን እሱረ ወውጉዘ።››*** ይህም ‹‹በማይገባ አይሰር፣ አያውግዝ። በማይገባ ቢያስርና ቢያወግዝ እርሱ ራሱ የታሰረና የተወገዘ ይሆናል።›› ማለት ነው። (ፍት፡ነገ፡አን፡፩) ፍትሐ ነገሥት አሁንም ***‹‹ወኩሉ ዘይረግም ይረግም ነፍሶ››*** ይላል። ይህም ‹‹የሚራገም ሁሉ ራሱን ይረግማል›› ማለት ነው። (ፍት፡ነገ፡አን፲፩) ማውገዝ መርገም መሆኑ ከላይ ተብራርቷል።

‹‹ሰይፍን የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ።›› የሚለው ቃል ከንቱ ግዝት ወደራስ

www.zeyeneta.com

እንደሚመለስ ያመለክታል። በክንቱ የሚያወግዙ የተወገዙ ናቸው እንደማለት ነው። ምክንያቱም ከላይ እንደተመለከትነው ሰይፍ ‹‹ግዝት›› የሚል መንፈሳዊና ረቂቅ ትርጉም አለውና። (ማቴ፳፮÷፶፪)

ተንኰለኛ ሰው በቆፈረው ጉድጓድ ራሱ ይወድቅበታል። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ወይወርድ ዓመፃሁ ዲቡ ድማሁ›› በአማርኛ ‹‹ዓመፃው ወደራሱ ይመለሳል።›› እንዳለው ማንኛውም ዓመፅ ወደራስ ሳይመለስ አይቀርም። ያለ አግባብ ማውገዝ በእግዚአብሔር ሥልጣን ማመፅና ያለ ዓላማው መጠቀም ነውና በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ሳይጎዳ አይቀርም።

ጸሎት ወደራስ ሊመለስ እንደሚችል አታውቅምን? አትጠራጠር ይህ ሊሆን እንደሚችል ቅዱስ ዳዊት ‹‹ጸሎቴ ወደ ብብቴ ተመለሰ›› ብሏል። (መዝ፴፬÷፲፫) ለክፉ አድራጊ ሰው ንስሐ እንዲገባ ካልሆነ በቀር ምሕረት ቢለምኑለት አይጠቅመውም። ይልቁኑም ጸሎቱ ተመልሶ ጸሎተኛውን ይጠቅመዋል። ለምሳሌ፡ ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት በሚደረግበት ጊዜ እነዚያ ሙታን በጸሎቱ ለመጠቀም ባልበቁ ጊዜ ጸሎቱ ከንቱ ሆኖ አይቀርም። ሙታኑ ባይጠቀሙም ፍትሐት ፈቺዎቹ ይጠቀሙበታል። ጸሎት ወደ ራስ ሊመለስ ይችላልና።

እንደዚሁም ሁሉ ሰዎች ባልበደለና ጥፋት በሌለበት ሰው ላይ ውግዘትና እርግማን እንደ በረድ ቢያዘንቡበት፣ እንዲጠፋና እንዲጎዳ ቢጸልዩበት ይህ ጸሎትና ውግዘት ተመልሶ አውጋዦቹንና

ረጋሚዎቹን ይጎዳል እንጂ ተወጋዡን አይነካም። ነቢዩ ‹‹*መጸለዮትየኒ ገብአ ውስተ ሕጽንየ*›› ወይም ‹‹ጸሎቴ ወደ ብብቴ ተመለሰ›› ያለው ስለዚህ ነው። (መዝ፴፬÷፲፫) ድንጋይን ወደ ላይ ቢያነጉት ወይም ቢወረውሩት ወደራስ እንደሚመለስ እንዲሁ ውግዘትንና እርግማንን የመሰለ ክቡድ ቃል (ከባድ ቃል) እግዚአብሔር በማይቀበለው መልኩ ወደ ላይ ቢልኩት ተመልሶ የሚጎዳው ራስን ነው።

ጸሎት ብቻ ሳይሆን ሰላምም ወደ ራስ ይመላሳል። ወንጌል ‹‹ሰላማችሁ ይመለስላችሁ›› ይላልና። ‹‹እርሱ ሰላማችን ነውና›› ተብሎ ስለተጻፈ የሰው ልጆች ሁሉ ‹‹ሰላም›› ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሐዋርያት በሚያስተምሩበት ጊዜ ወደ ቤት ገብተው ሰላምታ ይሰጣሉ። የሰላም ሰው ካለ ሰላማችው ያድርበታል። ከሌለ ግን ‹‹ሰላማችው ይመለስላችው›› ነበር። ይህ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የተገባላቸው ቃል ኪዳን ነበርና። (ማቴ፲÷፲፪-፲፫) ይህም ማለት ቃላቸውን ሰምቶ ባመነው ላይ የሐዋርያት ሰላም የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ያድርበታል። ቃላቸውን ሰምቶ ባላመነው ሰው ላይ ግን ለማደሪያነት አልበቃምና ኢየሱስ ክርስቶስ አያድርበትም። በሐዋርያት ብቻ እንዳደረ ይቀራል። ‹‹ሰላማችሁ ይመለስላችሁ›› ማለት ምሥጢሩ ይህ ነውና።

ከዚህ አስተምህሮ ስንነሣ ‹‹ሰላማችሁ ይደርበት›› ሲል ካህናት ቢያወግዙና የተወገዘው ሰው በእርግጥ የሚያስወግዝ ጥፋት ተገኝቶበት ከሆነ ያ ሰው ለመረገም የበቃ ነውና ‹‹እርግማናችሁ

www.zeyeneta.com

ይደርበት›› የሚል አንጻራዊ ትርጉም አለው። ‹‹ሰላማችሁ ይመለስላችሁ›› ሲል ደግሞ ካልሆነ ግን በማይገባ አውግዛችኋልና ‹‹እርግማናችሁ ወደራሳችሁ ይመለስ›› እንደማለት ይሆናል። ስለዚህ በማይገባ ማውገዝ ራስን ማውገዝ ነው። (ማቴ፲÷፲፪-፲፫)

እውነት ነው! እግዚአብሔር የባረከውን መርገምና ሚውገዝ ራስን መርገምና ማውገዝ ነው። ይህም ለአብርሃም በተሰጠው ቃል ኪዳን ይታወቃል። እግዚአብሔር አብርሃምን ‹‹ለበረከት ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ÷ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤›› በማለት ቃል ገብቶለታል። (ዘፍ፲፪÷፪-፫) በተመሳሳይ አገባብ የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ልጁን ሲባርክ ‹‹የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን የሚባርክህ እርሱ ቡሩክ ይሁን።›› ብሏል። (ዘፍ፳፯÷፳፱)

ኖኅ የወይን ጠጅ ጠጥቶ በሰከረ ጊዜ ልብሱን ጥሎ ወድቋል። በዚህ ጊዜ ካም የተባለው ልጁ እርቃኑን ስላየው ተሳልቆበታል። ይህን ያወቀ ኖኅ ከስካሩ በነቃ ጊዜ ልጁ ካምን በእርግማን ለመቅጣት አሰበ። ይሁን እንጂ ለመርገም ፈራ። ምክንያቱም ከጥፋት ውኃ በኋላ ከመርከብ ሲወርዱ እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቦቹን ስለባረካቸው ነው።

ከመርከብ ሲወርዱ ከተባረኩት የኖኅ ቤተሰቦች ውስጥ አንዱ ልጁ ካም ስለነበር እርሱን መርገም እግዘአብሔር የባረከውን እንደ መርገም ይሆናል። እግዚአብሔር የባረከውን መርገም ደግሞ በራስ ላይ እርግማንን ማምጣት እንደሆነ ኖኅ ጠንቅቆ ያውቃል። ይህ

የኖኅ ስጋት በዘመነ አብርሃም እጅግ ግልጥ ሆኗል። ቀደም ሲል ስለ አብርሃም ‹‹ለበረከት ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ÷ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤›› ተብሎ የተነገረው ቃል የኖኅን ፍርሃት ነፍስ የሚዘራበት ነው። ‹‹የሚረግሙህን እረግማለሁ›› የሚለው ቃል ለተራጋሚ ሰው አያስፈራውምን?

ኖኅ ልጁ ካምን ሳይቀጣው አላለፈውም። እርሱን መርገም ቢፈራም ልጁን ከነዓንን ረግሞበታል። ልጅን መርገም በተዘዋዋሪ አባትን መርገም ነውና በዚህ መንገድ ተቀጥቷል። ‹‹አንድ ጊዜ ተባርኬአለሁና የሚረግመኝ አይኖርም።›› እያሉ መመጻደቅ አይቻልም። እርግማን መግቢያ አያጣምና። ካም በቀጥታ ባይረገምም ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ በልጁ በኩል የመጣ እርግማን ሳይጎዳው አልቀረም። (ዘፍ፱÷፩-፳፭)

በተጨማሪም ሀብተ መርገም የነበረው በለዓምም እግዚአብሔር የባረከውን ሰው መርገም እንደማይገባ የሚያስረዳ ቃል ‹‹እግዚአብሔር የባረከውን እንዴት እረግማለሁ?›› በማለት በጥያቄ ካስቀመጠ በኋላ ትንሽ እልፍ ብሎ ደግሞ ስለ እስራኤል ‹‹የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን የሚረግምህም ሁሉ የተረገመ ይሁን።›› በማለት ግልጥ ቃል ተናግሯል። (ዘኁ፳፫÷፳፤ ፳፬÷፱)

እንዲያውም በለዓም እስራኤልን ከመርገም ይልቅ ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ባርኳቸዋል። በዚህ ጊዜ ባላቅ የተባለው የሞዓብ ንጉሥ እየተቆጣ ‹‹ጠላቶቼን ትረግምልኝ ዘንድ ጠራሁህ እነሆም ፈጽመህ

www.zeyeneta.com

ባረከሃቸው›› አለው። በለዓም ደግሞ ‹‹በውኑ እግዚአብሔር በአፌ ያደረገውን እናገር ዘንድ አልጠነቀቅምን›› ሲል መልሶለታል። (ዘኍ፳፫÷፲፪)

በማይገባ መገዘት የነፍስና የሥጋን ፈውስ ያሳጣል። እንዲህ በሚያደርጉ ሰዎች ላይ ምን እንደሚከሠት ሄኖክ ትንቢት ተናግሮባቸዋል። ‹‹እንዳትፈቱ ሁናችሁ የማይገባ ግዝትን ለምትገዝቱ ለእናንተ ወዮላችሁ ስለ ኃጢአታችሁም ድኅነት ከእናንተ ራቀ።›› (ሄኖ፷፮÷፲፰)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በማይገባ የሚገዝቱ ሰዎችን የሚመለከት የተግሣጽ ቃል ‹‹መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ›› ሲል ተናግሯል። (ማቴ፳፫÷፲፫)

በዚህ ንዑስ ርእስ ሥር የሰፈረው ትምህርት ያለ አግባብ ተወገዝን እያሉ ለሚንጨረጨሩ ሁሉ ተስፋ ነው። ያለ አግባብ ቢወገዙ ምን አስጨነቃቸው? እስከዚህ ድረስ በተረዳነው መሠረት ከእነርሱ ይልቅ የሚጎዳው አውጋዣቸው አይደለምን? ከራሳቸው ጥቅምና ስለስማቸው ከሚጨነቁ ይልቅ ላወገዛቸው ሰው ቢያዝኑለት ይገባቸው ነበር።

የተወጋዥ ወዳጆችም መቆጣትና መናደድ አይገባቸውም። ወዳጃቸው በሚገባ መንገድ ከተወገዘ ሊያዝኑለትና ከክፉ ግብሩ ተመልሶ ይቅርታ እንዲጠይቅ ሊመክሩት ይገባል። ያለአግባብ

ተወግዞ እንደሆነ ግን ክብር እንደሚያገኝበት አውቀው እርሱን ሊያጽናኑት እነርሱ ደግሞ ወዲያቸው ስለሚያገኘው ክብርና መንፈሳዊ ዋጋ ደስ ሊላቸው ያስፈልጋል።

በአግባቡ ለተወገዙ ሰዎች ያለአግባብ መቆርቆር ግን የአጋንንት ወደጅ ከመሆን አይዘልም። በእግዚአብሔር ሥራ የማይደሰቱ ሰይጣንንና ግብረ አበሮቹን የማያወግዙ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ ናቸውና።

በሃይማኖትና በምግባር ከተወገዙ ሰዎች መራቅ ይገባል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበላው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።›› በማለት በግልጽ ተናግሯል። (፪ተሰ፫÷፮) ይህ ቃል ቁርጥ ትእዛዝ እንጂ ምክር አይደለም። ‹‹እናዛችኋለን›› ይላልና። ከትእዛዝም ጥብቅ ትእዛዝ መሆኑን ደግሞ ‹‹በጌታች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም›› የሚለው ሐረግ ምስክር ነው። ይህ የሐዋርያው የብቻው ትእዛዝ ሳይሆን በዘመኑና ከእርሱ በኋላ የሚነሡ ቅዱሳን አበው ሁሉ ትእዛዝ ነው። ‹‹እናዛችኋለን›› ይላል እንጂ ‹‹አዛችኋለሁ›› አይልምና።

ምግባርና ሃይማኖታቸው ከከፋ ከኃጥአን፣ ከቀራጮችና ከአረመኔዎች ጋር እንዳንተባበር መጽሐፍ ቅዱስ አስጠንቅቆናል። (፩ቆሮ፭÷፱፣ ፲፭÷፴፫፣ ፪ዮሐ፲-፲፩፣ ፪ቆሮ፮÷፲፬-፲፯) ከክፉ ሥራችን አንመለስም ብለው በውግዘት የተለዩ ሰዎች ደግሞ ምድባቸው ከአሕዛብ፣ ከአረማውያን፣ ከኃጢአተኞች፣ ከዓመፀኞችና ከመናፍቃን

www.zeyeneta.com

ጋር ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ‹‹ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ›› የሚለው እንደእነዚህ ያሉትን ነውና። (ማቴ፲፰÷፲፯)

ሥራቸውና ክፋታቸው በግልጽ ከሚታወቅ ከአሕዛብና መምለክያነ ጣዖታት ይልቅ መጠንቀቅና አለመተባበር የሚገባው መናፍቃንን ነው። ከመናፍቃን በላይ ደግሞ ከተወገዙ ሰዎች መጠንቀቅ ይገባል። ምክንያቱም ከአሕዛብ ይልቅ መናፍቃን ከመናፍቃን ይልቅ ደግሞ የተወገዙ ሰዎች ተመሳስሎ የመኖር ሰፊ ዕድል ስላላቸው ነው። ተመሳስለው ከኖሩ ደግሞ ሌሎችን በቀላሉ ወደራሳቸው የጥፋት ጎዳና ይስባሉ።

በዘመነ ኦሪት እስራኤል ለምጽ ያለበትን ሰው እንዲለዩ ታዘዋል። ሙሉ በሙሉ በሰውነቱ ለምጽ ያለበትን ሰው ለይተው ሥርዓት ይሠሩበትና በከተማቸው ውስጥ አብሯቸው እንዲኖር ይፈቅዱለታል። ህንብርብር ወይም ዥንጉርጉር የሆነ እንደሆነ ግን በከተማ ለመኖር ዕድል አይሰጡትም ነበር። ሙሉ በሙሉ ሰውነቱ በለምጽ የነደደበት ሰው ደኅነኛ ሰው መስሎ ማታለል አይችልም። ህንብርብር ለምጻም ግን ለምጽ ያለበትን የሰውነት ክፍሉን በልብስ በመሸፈን ደኅነኛ ሰው መስሎ ሊያታልል ይችላል። (ማቴ፳ ትርጓሜ) እንደዚሁም ሁሉ አሕዛብ ክርስቲያኖችን የሚያታልሉበት ምክንያት የላቸውም። ክርስትና ከአሕዛብነት ጋር መመሳሰል የላትምና። መናፍቃንና በውግዘት የተለዩ ሰዎች ግን ‹‹እኛም እኮ እንደእናንተ ነን። ልብላችን ከልብላችሁ፣ ኃይለ ቃላችን ከኃይለ ቃላችሁ፣ ሃይማኖታችን ከሃይማኖታችሁ ጋር አንድ ነው›› እያሉ ምእመናንን ለማደናገርና ለማስካድ ይመቻቸዋል። ስለዚህ ከአሕዛብ ይልቅ መናፍቃንንና ውጉዛንን በሚገባ ለይቶ በማወቅ በክፉ ሥራቸው አለመተባበር ያስፈልጋል።

ምዕራፍ ሰባት

ውግዘትን ስለመፍራት

መልካም እየሠራህ በሐሰት ስትወገዝ ደስ ይበልህ፤ ዝለልም። ይህ ባንተ የተጀመረ አይደለም። ከቀድሞ ጀምሮ ያልተሰደበና ክፉ ስም ያልወጣለት ጻድቅ አይገኝም። በሐሰት ስትወገዝ ክፉ ስም እንደወጣልህ ያህል ዋጋ ታገኝበታለህና። (ሉቃ፮÷፳፪)

ክፉ ሥራ ሠርተህ በእውነት ስትወገዝ ግን ደንግጥ፣ እፈር፣ እዘን ንስሐም ግባ። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹*ኀፈሩኬ እምኔነ። ወደንግፀ*›› ይላልና። (ተግ ዘዮሐ አፈ፬) የውግዘት ዓላማውም ይኸው ነውና። የቀድሞ ክርስቲያኖች እንደዛሬ ሰው ሁሉ ይበድሉ ነበር። ነገር ግን ግዝትንና ቃለ ካህንን በመፍራት ከአሁን ዘመን በእጅጉ ይለዩ ነበር። መወገዝን የሚፈራ ካህን ማውገዝንም ይፈራልና በጥንቃቄ ያደርገዋል።

ግዝትን የሚፈሩ እግዚአብሔርን የሚያምኑና የሚፈሩ ናቸው። እግዚአብሔርን የማይፈሩ ግን ያስመስላሉ እንጂ ቃለ ካህንን አይፈሩም። ውግዘት የደረሰባቸውን መናፍቃንንና ግፈኞችን ባለሥልጣናት ታሪክ ስናጠና ፈጣሪን የማይፈሩ ሆነው ሳለ ነገር ግን ውግዘትን እንደሚፈሩና ክህነትን እንደሚያከብር ሰው ሲያስመስሉ እናገኛቸዋለን።

አርዮስ በሊቢያ ተወልዶ መንፈሳዊ ትምህርቱን በአንጾኪያ የተከታተለ ክርስቲያን ነበር። ትምህርቱንም እንደጨረሰ ወደ

www.zeyeneta.com

እስክንድርያ ተመልሶ መኖሪያውን በዚያ አደረገ። በዘመኑ ከነበረው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ከተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ የዲቁና ማዕረግ ተቀብሏል። ከዚህ በኋላ ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ባየው ራእይ መሠረት አርዮስ በክህደት ትምህርቱ ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ እንደሚያውክ ተረድቶ አውግዞታል።

ቀጥሎም ሁለቱን ተማሪዎቹን አኪላስንና አለእስክንድሮስን ጠርቶ ራእዩን በመንገር አርዮስን እንዳያስጠጉ አደራ አላቸው። እርሱም አርዮስን ከውግዘቱ ሳይፈታው በሰማዕትነት አርፏል። አኪላስ በመንበሩ ሲቀመጥ አርዮስ መጥቶ ስለተለማመጠው ባልንጀርነቱ በልጦበት የመምህሩን አደራ ወደ ጎን በማድረግ ከተቋቧለው በኋላ የቅስና ማዕረግ ሾመው። በዚህ ምክንያት ተቀሥፎ በቦታው ብዙ ሳይቆይ በአንድ አመቱ ሞተ። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ፹፰)

አኪላስ ከሞተ በኋላ በቦታው የተተካው አለ እስክንድሮስ ነው። ከአኪላስ በተለየ ሁኔቴ እለእስክንድሮስ የአርዮስን እንቢተኛነት ተመልክቶ ደግሞ አውግዞታል። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ፻፯)

አርዮስ በክህደቱ በተደጋጋሚ በተወገዘ ጊዜ ‹‹ወፈ ገዝት›› ብሎ በመመጻደቅ አርፎ አልተቀመጠም። ከግዝት ለመፈታት የተቻለውን ሁሉ አድርጓል። አንድ ጊዜ ጠፍቶ ይከርምና ‹‹ከአባ እገሌ ዘንድ ሄጄ ተፈትቼ መጣሁ›› ይል ነበር። ሌላ ጊዜ ደግሞ

‹‹አምኖለሁና ፍቱኝ›› ብሎ ይለማመጣል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ምቹ ሁኔታ በተፈጠረ ቁጥር በኃይልና በማስገደድ ከግዝት ለመፈታት ሲጥር ይታያል። በአብሮ አደግነትና በባልንጀርነትም ተለሳልሶ በመቅረብ ከግዝቱ ለመፈታት ሞክሯል። ወዳጁ የነበረው አኪላስም ለመቅሠፍት ሞት የተዳረገው በዚህ መንገድ ተጭበርብሮ አርዮስን ከግዝቱ ስለፈታው እንደሆነ መጻሕፍት ይተርካሉ። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ፻፷)

ይህ ሁሉ የሚያሳየን አርዮስ ግዝትን የሚፈራ ሰው እንደነበር ሳይሆን ከግዝት መፈታቱ በአንድ መንገድ አላማውን ለመፈጸም እንደሚረዳው ያምን እንደነበር ነው። ከተወገዘ በኋላ በሚናገረው እምነት ካጣና በሰዎች ዘንድ ከተጠላ ይህን ዘዴ አማራጭ ማድረጉ የሚያስደንቅ አይደለም። አርዮስ በእውነት ግዝትን የሚፈራ ሰው ቢሆን ኖሮ ከስሕተቱ ይመለስ ነበር። በዚህም ላይ ባወገዙት ሰዎች ላይ ምቹ ጊዜ ባገኘ ቁጥር ነገር አይሠራባቸውም ነበር። እርሱ ግን ያወገዙትን ሲያወግዝና ሲያስወግዝ፣ ስማቸውንም ሲያጠፋ ዘመኑን ፈጽሟል።

በዚህም ዘመን የአርዮስን ትምህርቱን ብቻ ሳይሆን ጠባዩንም በመላበስ የሚያጭበረብሩ በርካታ ሰዎች ይገኛሉ። ከዚህ ይልቅ ግን ቢቻል ግዝትን ፈርቶ ራስን ከተሳሳተ ትምህርትና ከምግባረ ብልሹነት መጠበቅ የበለጠ ይጠቅማል። ክህነትንና ግዝትን ንቆና ተደፋፍሮ ሌላውን ሰው ማደፋፈር ድርብ ጥፋት ነው።

www.zeyeneta.com

ግዝትን ፈርቶ የተጨነቀ ስለመምሰል ከአርዮስ ቀጥለን የምናነሣት ሴት ንግሥት አውዶክስያ ናት። ንግሥት አውዶክስያ መፍቀሪተ ንዋይ ነበረችና የድሀ መበለትን ዓፀድ በግፍ ነጠቀች። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የድሆች ጠበቃ ነውና እንድትመልስ ለማድረግ ብዙ ጥረት አደረገ። ሳይሆን ሲቀር በመጨረሻ ንግሥቲቱን ከምእመናን አትገናኚ፣ ከቤተ ክርስቲያን አትግቢ፣ ሥጋ ወደሙን አትቀበዪ ብሎ አወገዛት። በዚህ ጊዜ ንግሥቲቱ ደንግጣ፣ አዝናና ተቆጥታ ወደ ጳጳሳቱ ወደ ቴዎፍሎስና ወደ ኤጲፋንዮስ መልእክት ልካለች።

ይህ ድርጊቷ ቃለ ውግዘትን የምትፈራ ቢያስመስላትም ሌሎች እርምጃዎቿ በሙሉ ደፋርነቷን ያሳያሉ። ከውግዘቷ ካልተፈታች የዲዮቅልጥያኖስን ዘመን መልሳ እንደምታመጣውና ክርስቲያኖችን እንደምታጠፋ ዝታ ነበር። ውግዘትን የሚፈራ እንዲህ ያስባልን? በዚህም ላይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እንዲያወግዙ በጥፋታቸው ከክህነት የተሻሩ ወሮበላ ሰዎችን አሰባስባ ዮሐንስ አፈወርቅን እንዲያወግዙ አድርጋለች። ይህም የምትገዛውን ሕዝብ ለማጭበርበር ካልሆነ በስተቀር ሃይማኖት እንደሌላት የሚያሳይ ድርጊት ነው።

ብዙዎች ደግሞ ቃለ ካህንንና ውግዘትን በመፍራት ምላሌ የሆነበት ሁኔታ አለ። በቅዱሳት መጻሕፍት እንኳን ሥጋ ለባሽ ሰውና መላእክትም ለካህን ቃል ሲገዙ እንመለከታለን። ቅዱስ

ዮሐንስ አፈወርቅ ከመንገድ አግኝቶ የገዘተው መልአከ ሞት ለዓሥር አመት ያህል ሳይንቀሳቀስ ቆሞ ተገኝቷል። ይህም ቃለ ካህን ምን ያህል የተፈራና የተከበረ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ ምእመናን ካህናትን እንደ ንጉሥ ቦሚገባ ሊፈሯቸው እንደ አባት ሊያፍሯቸው ይገባል። ምእመናንን የራሳቸውን ቃል እንደ ቃለ መሐላ፣ የካህንን ቃል እንደ ግዝት፣ ግዝትን ደግሞ እንደ ኩነኔ ሊፈሩ ይገባቸዋል።

በዘመናችን ምእመናን ቃለ ካህንን ፈርተውና አክብረው ‹‹ቄስ(አባ) እገሌ አወገዙኝ አማልዱኝ›› ብለው ሲመጡባቸው ጉዳዩን መርምሮ መፍትሔ ከመፈለግና ለማግባባት ከመሞከር ይልቅ ‹‹ሄዲያ እርሱ ደግሞ ወፈ ገዘት ነው። እኔ ፈትቼ(ሻ)ሃለሁ ምን አስጨነቀ(ሽ)ህ›› የሚሉ ክህነትንም የሚያቃልሉ ጎርቴማን (ጎስቋላ) ካህናት ቁጥር ጥቂት አይደለም። ይህም ስለ ምሥጢረ ክህነትና ስለ ውግዘት የምእመናንን ያህል እንኳን በቂ ግንዛቤ ሳይኖር ሲቀር የሚከሠት ችግር ወይም ደፋርነት ነው።

ሊቀ ጳጳሳቱ ኤጲፋንዮስና ቴዎፍሎስ ንግሥት አውዶክስያ ‹‹ቅዱስ ዮሐንስ በማይገባ አወገዘኝ›› ብላ ብትመጣባቸው ሊሸመግሏት ጥረት አደረጉ እንጂ ‹‹እኛ ፈትተንሻል›› እያሉ በማይገባ መንገድ አላጽናኗትም። ወይም ቅዱሳንና ትሑታን ነበሩና ‹‹እርሱም ጳጳስ እኛም ጳጳሳት›› እያሉ አልተመጻደቁም። ስለዚህ ምእመናን ክህነትንና ቃለ ካህንን እንዲያከብሩ ካህናት ራሳቸው በበለጠ ክህነትን እያከበሩ ማሳየትና አርአያ መሆን አለባቸው።

www.zeyeneta.com

በአግባቡ የተደረገውን ግዝት ‹‹ወፈ ገዝት›› ብሎ በሚያቃልል ሰው ላይ ***‹‹ናሁ እግዚእነ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ይሜሰጥ ለኵንኖቱ››*** ***ይላል።*** (ተግ ዘዮሐ አፈ፬) ይህም ‹‹ክብር ይግባውና ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርድበታል›› ማለት ነው። በአጠቃላይ ተገቢ ግዝትን እንደ ድርና ማግ ወይም በቀላሉ እንደሚበጠስ ክር አቃለው ‹‹ግዝት ብዝት›› የሚሉ ሁሉ ከዚህ ቅጣት ነጻ አይደሉም። ውግዘት መለኮታዊ ማሠሪያ አምላካዊ ሰይፍ ነውና።

አንዱ ያወገዘውን በሌላው የመፈታት ጽንሰ ሐሳብ አርዮስ ሲጨንቀው በጓሮ በር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊያስገባው የሞከረው እንጂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደለም። አርዮስ በተወገዘ ጊዜ ለጊዜው አካባቢ በመቀየር ጥፍት ብሎ ይከርማል። በኋላ ይመለስና ‹‹ወፈ ገዝት›› እለእስክንድሮስ ቢያወግዘኝ ተፈትቼ መጣሁ እያለ ያጭበረብር ነበር። በዚህ መንገድ ቅስና እስከ መቀበል ደርሶ ነበር። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ፻፯)

ቄስና ጳጳስ በአኗኗር ዘይቤና በአስተዳደራዊ ጉዳይ ካልሆነ በቀር በማሰርና በመፍታት ሥልጣን አይበላለጡም። ጳጳስ የሚያስተሠርየውን ኃጢአት ሁሉ ካህንም ያስተሠርያል። ጳጳስ የሚያስረውን ሁሉ ካህንም ማሰር ይችላል። ነገር ግን ቄስ መንፈሳዊ ሹመት መስጠት አይችልም፣አይክንም። ጳጳስ በሚሾምበት ጊዜም እንደ ሿሚ ጳጳስ እጁን ለመጫን አይበቃም።

ይህን ልዩነትና አንድነት በመጠኑም ቢሆን መግለጥ ያስፈለገው ቄስ ያወገዘውን ባለበት ሁኔታ ጳጳስ ሊፈታው የሚችል የሚመስላቸው በርካቶች ስላሉ ነው። በእርግጥ ክህነት አንዲት ናትና አንድ ካህን ገዝቶ ቢሞትና ከእርሱ ሞት በኋላ ተወጋዡ ንስሐ ገብቶ ቢመለስ ሌላ ካህን ሊፈታው ይችላል። ነገር ግን አውጋዡ በሕይወት እያለ ተወጋዡ ቢመለስ ከውግዘት መፍታት ያለበት አውጋዡ ራሱ ነው።

አርዮስ እንኳን ያወገዘው ሊቀ ጳጳሱ ጴጥሮስ ሳያርፍ ፍታኝ ብሎ ወደ አኪላስ አልመጣም። የአርዮስ የልቡ ክህደትና አልታረም ባይነቱ አስቀድሞ በራእይ ባይታወቅና በሚገባ በንስሐ ተመልሶ ቢሆን ኖሮ ያወገዘው ሊቀጳጳሱ ጴጥሮስ በሕይወት እስከሌለ ድረስ አኪላስ ውግዘቱን መፍታቱ ዕዳ አይሆንበትም ነበር። አውጋዡ በሕይወተ ሥጋ ከሌለ ሌላ ካህን ውግዘትን ሊፈታ ይችላልና።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ስምንት

በዝምድና፣ በጥቅም፣ በባልንጀርነት እየተደለሉ፣ በኃይል እየተገደዱ ስለማውገዝና ስለመወገዝ

ነገሥታትና ሹማምንት የወደዱት እንዲወደስ የጠሉት እንዲወገዝ መፈለጋቸው ድንቅ ነገር አይደለም። እነርሱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይደሉምና ጥብቅናቸው ለሥልጣናቸውና ለጥቅማቸው ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊያን ሹማምንት ግን የእነዚህ ዓለማዊያን ነገሥታት ቀኝ እጅ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ አለባቸው።

አባ ጎርጎርዮስ በታሪክ መጽሐፋቸው ‹‹በቤተ ክርስቲያን አለመግባባት በተፈጠረ ቁጥር ጠቡን እያጋነኑ የሚያባብሱት ነገሥታቱ ነበሩ›› በማለት ቁልጭ አድርገው ጽፈዋል። መጽሐፉን ብታነቡት ይህን ድንቅ እውነት በተለያየ አገላለጥ ሲደጋገሙት ታገኙታላችሁ። የዚህችን ዘማ ዓለም (አመንዝራ ዓለም) የተንኮል አካሄድ የማያስተውልና ያልተማረ ካህን ሲገኝ ደግሞ ነገሥታቱ ዓላማቸውን ሳይወጥኑ ለመፈጸም ምቹ ዕድል ያገኛሉ። እንደ እነ ቅዱስ አትናቴዎስና እንደእነ ዮሐንስ አፈወርቅ ያለ ሲገኝ ደግሞ በእሥራትና በግርፋትም አይንበረከክላቸውም። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፻፸፩ እና ፻፸፯)

ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ መጠመድ እንደማይገባ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስጠንቅቋል። (፪ቆሮ፮፥፲፬) ስለዚህ በሃይማኖት ቸለያይቶ ጥልቅ ወዳጅነት አያዋጣም። በሃይማኖት አንድ ሳይሆኑ ጋብቻ ደግሞ ከመወዳጀትም በላይ የከፋ ነው። ከዚህም የሚከፋው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሃይማኖትን ከሚጻረር ሥነ መንግሥት ወይም ፖለቲካ ጋር መተሳሰር ነው። በባሏ የማትወሰን ሴሰኛ ሴትና ፖለቲከኛ የሃይማኖት መሪዎች አንድ ናቸው።

መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት የለበትም። ነገር ግን ይህ ሁል ጊዜ ሲፈጸም አይገኝም። ቤተ ክርስቲያን ይህ እንዲከበርላት አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለባት። ሃይማኖታችን ብሔራዊ ሃይማኖትነቷ በመንግሥት እውቅና በነበረው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከቤተ መንግሥት ጋር የነበራት ቁርኝት ጠቀማት ባይባልም ግንኙነቱን ለመኮነን በቂ መንፈሳዊ መሠረት ላይገኝ ይችላል። ነገር ግን መንግሥት ከሃይማኖት ልዩ መሆኑ በሚታወጅበት በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ወደ ፖለቲካ ለመቅረብ ብትጋፋ ያሳፍራል። ቤተ ክርስቲያን ስለ ሥነ መንግሥት ያላት ትምህርት ግልጥ በመሆኑ አንዳንድ አገልጋዮቿ ወደ ፖለቲካው ቢያዘመሙ የግል አቋማቸው እንጂ የቤተ ክርስቲያን መርሕ ሆኖ አይደለም።

www.zeyeneta.com

ቤተ ክርስቲያን ከፖለቲካ መለየት አለባት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ሊሆን ያስፈልጋል። እንደ ተቅዋም ጉዳዮችዋን በመከታተል ማስከበርና ግዴታዎቿንም መወጣት ይኖርባታል። ማንኛውም ዜጋ የሀገሬ ጉዳይ አይመለከተኝም ማለት እንደማይችል ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ተቋም ከአንድ ግለሰብእ ብላይ ሀገራዊ ጉዳይ ይመለከታታል። ስለዚህ ከፖለቲካ መለየት ማለት ከዓለም መውጣት ማለት ሳይሆን ዓለማዊውን እንደ ዓለማዊ ጉዳይነቱ በልክና በፈለጥ እያከናወኑ ዘብ ለቆሙለት መንፈሳዊ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው።

ቄሳውያን ነገሥታትና ሹማምንት አንድ ጊዜ በጥቅምና በሹመት በማታለል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በኃይልና በጉልበት በመደለልና በማስፈራራት ካህናትን የግል ፍላጎታቸው ማስፈጸሚያ ያደርጋሉና ካህናት ምን ጊዜም ሰማያዊ ንጉሥን ብቻ መፍራት ይኖርባቸዋል። ‹‹እንደንጉሡ አሳንብሉ›› እንደሚባለው ጊዜ የወለደውን ንጉሥ የወደደውን በመከተል የማይወገዘውን ቢያወግዙ ወይም ደግሞ መወገዝ ያለበትን ሳያወግዙ ቢቀሩ ወይም ሊደገፍ የማይገባውን ቢደግፉ እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ በፈጣሪ ዘንድ ራሳቸው ሳይገሠጹ አይቀርም። ለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ ንጉሡ ዖዝያንን ባለመገሠጹ የደረሰበትን ማንሣት ብቻ በቂ ነው። (ኢሳ፮፥፩)

ይህን የሚያደርጉ ዓላውያን ነገሥታት ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። መንፈሳዊያን መሪዎችም በተመሳሳይ መንገድ በአስተዳደር

የሚበልጧቸውን ሰዎች የማይገባ ሥራ ሊያሠሯቸው ይሞክራሉ። በዚህ ጊዜ ሕሊናንና እግዚአብሔርን ብቻ በመፍራት የሚገባውን ብቻ ማድረግ ከማንኛውም ሰው ይጠበቃል። ለጥቅም ብቻ ሲሉ የማይገባን ነገር ‹‹ምን ላድርግ? የበላይ ትእዛዝ ነው።›› እያሉ ማከናወን ከተጠያቂነት አያድንም። ሕሊናን ይሰብራል፤ በፈጣሪ ዘንድ ያዋርዳል። ፍቅረ ምእመናንንም ያሳጣል።

ባላቅ እስራኤልን ለማስረገም ብዙ ዘዴ ተጠቅሟል። በመጨረሻ በለዓምን በጥቅምና በዋጋ መደለሉ ተሳክቶለታል። ይህ ሰፊ ታሪክ ለትምህርትና ለተግሣጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቧል። በለዓም ከሞአብ ንጉሥ የተቀበለው የኃጢአት ገንዘብ የ‹‹ዓመፅ ደመወዝ›› ተብሏል። (፪ጴጥ፪÷፲፭) ስለ ሥጋዊ ጥቅም፣ ሹመትና ገንዘብ ብለው በማይገባ ለሚያወግዙ ካህናት ሊጠቀስ ይችላል።

ኤጲፋንዮስ ከዮሐንስ አፈወርቅ ጋር አብሮ ሲማር ያደገ ወዳጁ ነው። ለሦስት ወር ያህል ንግሥት አውዶክስያን ክግዝት እንዲፈታት እየማለደው አብሮት ሰንብቷል። ይሁን እንጂ ገጽ አይቶ የማያዳላ ዮሐንስ አፈወርቅ ባልንጀርነቱን አይቶ ልመናውን በመስማት ግዝቱን አልፈታም። ከግዝት መፈታትና ነጻ መሆን ከክፉ ሥራ ተጸጽቶ በመመለስ እንጂ በዝምድናና በባልንጀርነት የሚገኝ ነገር አይደለምና። አርዮስ ሳይመለስ ከግዝቱ የፈታው ወዳጁ አኪላስ የደረሰበትን የመቅሠፍት ሞት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጠንቅቆ ያውቃል።

www.zeyeneta.com

አርዮስ ተወግዞ ከተጋዘ ከሁለት ዓመት በኋላ አርዮሳዊያኑ እነአውሳብዮስ ዘኒቆሚዲያ የቆስጠንጢኖስን እኅት ለመኗት። እርሷም ሄዳ ወንድሟን ማለደችው። በዚህ ጊዜ በሲኖዶስ የተወሰነውን ውሳኔ ወደ ጎን በመተው ቆስጠንጢኖስ አርዮስ ከግዞት እንዲመለስና ከግዝት እንዲፈታ መልእክት አስተላለፈ። ያጋዘው ራሲ ነበርና ከግዞት መመለሱ ችግር አልነበረውም። ነገር ግን ከግዝት እንዲፈታና ክህነቱ እንዲመለስለት ማዘዙ በቅዱስ አትናቴዎስ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ይህም ጉዳይ በቆስጠንጢኖስና በአትናቴዎስ መካከል የከረረ ጠብ እንዲፈጠር አድርጓል። አትናቴዎስ የንጉሡን ቃል ሳይፈራ ለቤተ ክርስቲያን አለኝታነቱን አሳይቷል።

ንግሥት አውዶክስያም በጥፋቷ በተወገዘች ጊዜ ጥፋቷን ከማረም ይልቅ ያወገዛትን ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ‹‹ምክንያት ፈልጋችሁ ከክህነቱ ሻሩት›› ብላ አዛለች። ነውረኞችና በደለኞች ሰዎቹ ቃሏን ፈጽመውላታል። ዛሬም ቢሆን ሹማምንት ያዘዟቸውን ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢር ጋር ሳያገናዝቡ የሚፈጽሙ ተመሳሳይ ሰዎች አይጠፉም። ጉዳዩ ጥፋት መሆኑን ቢያውቁም ከእምነት ጉድለት የተነሣ እንደ ይሁዳ ገንዘብና ጥቅም ሸተው፣ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ፈርተው የማይገባውን ወደ ማድረግ ያዘነብላሉ።

መወገዝ ያለበትን ሳያወግዙ ስለመቅረት

(ቸልተኝነት)

ሥልጣነ ክህነት ማስፈራሪያ ሳይሆን ሥራ መሥሪያ ነው። ክፉ ነገርን ከሥሩ ቆርጦ የሚጥል መለኮታዊ ሰይፍ ነውና። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ባለሥልጣን በአስፈላጊ ጊዜ ሳይጠቀምበት በከንቱ ሰይፍ አይታጠቅም። ‹‹ባለሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል። ለመልካም ነገር ላንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ። ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።›› (ሮሜ፲፫፥፫-፬) ስለዚህ ካህናት እንደ ንቁ ወታደር ተግተው መንጋቸውን መጠበቅና የጠላትን ወጥመድ በሥልጣናቸው መቆራረጥ አለባቸው። ሥልጣነ ውግዘት ካህናት የሚታጠቁት መንፈሳዊ ሰይፍ ነውና።

መወገዝ ያለበትን ሳያወግዙ መቅረት በክፉ ሥራው መተባበርና ማበረታታት ነው። ጥፋትን በቸልታ ማለፍ ኃላፊነትን በአግባቡ እንዳለመወጣት ይቆጠራል። መገሠጽና ማውገዝ ተገቢ በሆነበት ቦታ ቸል ብሎ መቀመጥ በታሪክ፣ በሕሊናና በፈጣሪ ዘንድ ተወቃሽነትን ያስከትላል። ስለዚህ ሳያስቀጣ አይቀርም።

www.zeyeneta.com

ካህኑ ዔሊ ልጆቹን ስላልከለከለ ማለትም አውግዞ ስላልየ እግዚአብሔር ፈረደበት። (፩ሳሙ፪፡፳፬፡ ፪፡፲፫-፲፩) ነቢዩ ኢሳይያስም ንጉሡ ያዝያንን በመፍራት ሳይገሥጸው ስለቀረ ራሱ በለምጽ ተገሥጿል። (ኢሳ፮፡፩) አባት ልጁ ጥፋት መሥራቱን ካወቀ በአግባቡ እንዲቀጣው ታዘዘል። (ምሳ፲፫፡፳፬፡ ፳፱፡፲፯) ነገር ግን ንጉሥ ዳዊት ነፍሰ ገዳይ የሆነ ልጁን ሳይፈርድበት ስለቀረ በዘሪያው ልጁ ከዙፋኑ ተባረል። (፪ሳሙ፲፫፡፳፰፡ ፲፬፡፳፰-፴፫፡ ፲፭፡፲፫-፲፯) ማኅበራት አባሎቻቸውን፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን፣ የነፍስ አባቶች ልጆቻቸውን፣ የመገሠጽና የመቅጣት ኃላፊነት አለባቸው። ይህንንም መፈጸም የግድ ያስፈልጋል። ከመፈጸምም ቢቀሩ ተወቃሾችና ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

ውግዘትን ስለሚያስከትል የዐመፅ ዓይነት

አንድ ሰው በውግዘት የሚለየው በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ያላመነ ሲሆን ብቻ አይደለም። በገዛ ፈቃዱ ሥርዓትን ያፈረሰ ሰው በውግዘት ሊለይ ይችላል። ስለዚህ የውጭና የውስጥ መናፍቃን እንደሚሉት ሥርዓትን መጠበቅና አለመጠበቅ ከጽድቅና ከኩነኔ ጋር የማይገናኝ ተራ ጉዳይ ሳይሆን በውግዘት የሚያስለይ ከባድ ጥፋት ነው።

ሀ. አለመታዘዝ ያስወግዛል። ‹‹እናንተን የጣለ እኔን ጣለ›› እንደተባለው ካህናትን የሾመ ፈጣሪ በመሆኑ ካህናትን አለመስማት ፈጣሪን አለመስማትና አለመታዘዝ ነው። አለመታዘዝ ሊያስወግዝ

እንደሚችል ***‹‹ወእመ ኢተአዘዘ ይትወገዝ መኑሂ በሕገ ቤተ ክርስቲያን››*** ያለው ቃል ያስረዳናል። ይህም ‹‹የማይታዘዝ ማንም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ይወገዛል።›› ማለት ነው። (ተግ ዘዮሐ አፈ፬)

ለ. ሥርዓት የማያከብር ከቤተ ክርስቲያን እንዲለይ ሐዋርያት በመልእክታቸው ጽፈዋል። ቃሉም ‹‹ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።›› የሚል ነው። (፪ተሰ፫፡፮) በዚህ ቃል መሠረት ‹‹ወንድሞች›› የተባሉ ምእመናን ጥፋተኛውን ወንድም እንዲለዩት ታዘዙ። የምእመናን ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ከ‹‹ወንድሞች›› መለየት ከቤተ ክርስቲያን መለየት መሆኑ ግልጥ ነው። እነርሱ ተለዩት ማለት እርሱም ከእነርሱ ይለያል። መለያየት በሁለቱም ወገን ያው ነውና።

ሐ. ከሕገ ቤተ ክርስቲያን በወጣ መንገድ ስለሞቱ ሰዎች ማዘን በውግዘት የሚያስለይ መናፍቅነት ነው። ስለሞተ ሰው የሚደረግ መራራ ኃዘን ተስፋ ትንሣኤን መጠራጠር ነውና። ይህን የሚያደርጉ አስቀድሞም የተወገዙ ናቸው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በተግሣጽ መጽሐፉ ***‹‹አንሰኬ እክልኦ በዊኦ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ነዋኅ መዋዕለ ለዘይገብር ከመዝ። በከመ እክልኦ ለመምለኬ ጣዖት።››*** ብሏል። ይህም በአማርኛ ‹‹እኔም እንዲህ የሚያደረገውን ሰው መላ ዘመኑን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ ከምእመናንም

www.zeyeneta.com

እንዳይገናኝ ጣያት አምላኪውን እንደምከለክል እከለክለዋለሁ፤ እለየዋለሁ።›› ማለት ነው። ይህ የቅዱስ ዮሐንስ ቃል ሥርዓት በጣሱ ሰዎች ላይ የተላለፈ ቃለ ውግዘት ነው።

መ. በመጽሐፈ ቅዳሴ ላይ «በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ፤ የቅዳሴው ጸሎት እስኪፈጸም ባይታገሥ፤ ከቁርባንም ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይለይ። የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፤ የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምንም ፈቃሏልና፤ ሐዋርያት በሰኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን።» የሚል የመግቢያ ጸሎት ይገኛል።

ሠ. ሰው በምግባር ሕፀፅም ሆነ በሃይማኖት ክህደት ሊወገዝ ይችላል። አባ አብርሃም ሶርያዊ መማለጃ የሚቀበሉትንና ዕቁባት ያሉአቸውችን ሰዎች ዕቁባቶቻቸውን እንዲተዉ ክፉ ልማዳቸውን ያርቅ ዘንድ ገዝቷል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንግሥት አውዶክስያን ደሀን ስለበደለች ስለክፉ ምግባሯ ገዝቷታል። (ስንክ ዘታኅሣሥ ድርሳን ዘዮሐንስ የታሪክ ዓምድ) ይሁን እንጂ ቶሎ እርምጃ የሚወሰደው ጥፋቱ የሃይማኖት ሆኖ ሲገኝ ነው።

ረ. ‹‹ጌታችንን የማይወደው›› እና ‹‹ልዩ ትምህርት የሚያመጣ›› ሁሉ የተወገዘ ነው። (፩ቆሮ፲፮÷፳፪፤ ገላ፩÷፰) ‹‹ጌታችንን የማይወደው›› ማለት ምግባር ያጎደለ ማለት ነው። ‹‹ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ›› ስለተባለ ያልወደደ አይታዘዝምና ምግባር ሊኖረው አይችልም። (ዮሐ፲፬÷፲፭) ‹‹ልዩ ትምህርት

የሚያመጣ›› ደግሞ ከቀድሞው ሌላ መሠረት የሚመሠርትና በአበው ትምህርት፤ ወግና ምሳሌነት የማይሄድ በአጠቃላይ ሥርዓት የሚያፈርስ ማለት ነው። (፪ተሰ፪÷፮)

ከዚህ በላይ ከ ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ረ›› በሰፈሩት ነጥቦች አንድን ሰው ሊያስወግዙት የሚችሉ ጥፋቶች በሙሉ ተዘርዝረዋል ማለት አይደለም። የሰው አስተሳሰቡም ሆነ ሥራው ውስብስብና ከጊዜ ጋር የሚሄድ ረቂቅ ነው። ስለሆነም የሚያስወግዙ ክፉ ምግባራትን በሙሉ መዘርዘርና ወሰኖ ማስቀመጥ አይቻልም። ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ጥቅል ሐሳቦች ናቸው። አንድ ሰው የሚሠራቸው ክፉ ሥራዎች ከተዘረዘሩት ውስጥ በአንዱ ሊፈረጁ ወይም ተካተው ሊቆጠሩ ይችላሉ።

ማጠቃለያ መልእክት

ቤተ ክርስቲያናችን ከእኅት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የበለጠ ተቀራርቦ ለመሥራት ጥረት እያደረገች ባለችበት በአሁኑ ወቅት በውስጥ ልዩነትን ለማምጣት መሞከር እጅግ የሚያሳዝን ሥራ ነው። የአሕዛቡንና የመናፍቃኑን የተጠናከረ እንቅስቃሴ የተመለከተና መንፈሳዊ ልቡና ያለው ሰው አንድነቱን ለማጽናትና ይጥራል እንጂ እርሱ ራሱ መለያየትን አያመጣም።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መለያየትን አይወድም። የ‹‹መልካሙ እረኛ ምዕራፍ›› ብለን በምንጠራው በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ አሥር ላይ ቤተ ክርስቲያን አንድ እረኛ

www.zeyeneta.com

አንድ መንጋ እንድትሆን የሚፈልግ መሆኑ በግልጽ ተጽፏል። የመንጋውም እረኛ እርሱ ራሱ ነው። (ዮሐ፲፥፩-፲፮፣ ፲፯፥፳፪) በተጨማሪም በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አሥራ ሰባት ላይ ስለ ደቀመዛሙርቱ ስለ ሐዋርያትና በአጠቃላይ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ወደ አባቱ እንዲህ ሲል አመልክቷል። ‹‹እኛ አንድ እንደሆን አንድ ይሆኑ ዘንድ›› በእርግጥ እንደ አብና እንደ ወልድ ያለ ምሥጢራዊና ባሕሪያዊ አንድነት በየትም ሊኖር አይችልም። ይሁን እንጂ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተመኘላት አንድነት ይህ ዓይነቱን አንድነት ነበር።

ካህናት ጥፋተኛን ለይተው በሚያወግዙበት ጊዜ ሥራውን በቅዱሳት መጻሕፍት መዝነው ነው። የሚመለከቱበትም አቅጣጫ አንድ ምእመን ያንኑ ጉዳይ ከሚመለከትበት አቅጣጫ ጋር አንድ ላይሆን ስለሚችል ምእመናን በግል አስተሳሰብ ተመርኩዘው የሚሰጡት አስተያየትና ትችት ልክ የማይሆንበት ብዙ ጊዜ ይኖራል። ከዚህም በተጨማሪ በውጭ ሆኖ ከሚታዘብ ማንኛውም ሰው ይልቅ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉት ወይም የጉዳዩ ባለቤቶች ማለትም አውጋዡና ተወጋዡ የበለጠ ስለሚተዋወቁ ስለትክክለኝነታቸው ለፈጣሪና ለሕሊናቸው መተው ከምእመናን ይጠበቃል።

ሙሴ የፈርዖን የልጅ ልጅ እየተባለ ቢያድግም በትውልዱ እስራኤላዊ ነበር። ይህንንም እንዲያውቅ እናቱ በጥንቃቄ

አስተምራዋለች። ካደገ በኋላ አንድ ግብጻዊ እስራኤላዊውን በኃይል ሲበድለው ተመለከተና ተበቅሎ በመግደል ቀብሮታል። ሌላ ቀን ደግሞ ሁለት እስራኤላዊያን እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ አይቶ በማንም ሊፈርድ ስላልቻለ ሊያስታርቃቸው ቀረበ ቢሆንም ንቀውና አቃለው አባረሩት። ፈጣሪ ግን እንደናቁት እንዲቀሩ አላደረገም። ወደ ምድረ በዳ ከተሰደደ በኋላ ብዙ ትምህርትና ልምድ ቀስሞ በመንፈሳዊ ሕይወትም ጎልምሶ ተመለሰ። ያን ጊዜ የናቁት ሁሉ አክብረው ተቀበሉት። (ዘፀ፪፥፲፩-፳፭)

ዛሬም ቢሆን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን አጠንክሮ መምራት የሚፈልጉ ምእመናን ማድረግ ያለባቸው ይህንን ነው። የተገለጠ ክህደት ያለባቸውን መናፍቃንን ቤተ ክርስቲያን አውግዛ ስትለያቸው ሙሴ ግብጻዊውን ገድሎ እንደ ቀበረው ያህል ይቆጠራል። ስለዚህ ምእመናን ያንን የተወገዘውን ክፉ ሰው እንደ ሞተ ቆጥረው በምንም ነገር እንዳይተባበሩት መሆን አለባቸው።

የታወጀው ውግዘት ግልጥ ሳይሆን ሲቀርና ሕሊናችን ለመቀበል ሲጠራጠር ወይም ሲፈተን ደግሞ ሐሜትንና ፍርድን ትቶ ወደ ፈጣሪ መጸለይ ይገባል። ሙሴ ወንድማማቾቹ ሲጣሉ ምንም ለማድረግ አልሞከረምና። ይህ ጉዳይ ለጊዜው ከዐቅሙ በላይ ነበር። ይልቅ የራሱን መንፈሳዊ ሕይወት አጠናክሮ ገፋበት። እስራኤላዊያኑ ‹‹በእኛ ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን ሾመህ›› እንዳሉት መስፍን ሆኖ ሲመጣ በክብር ተቀበሉት። የሚመኩበትም ሰው ሆነ።

www.zeyeneta.com

ስለዚህ ከምእመናን ዕውቀትና ችሎታ ውጭ የሆነ ማንኛውንም ነገር ፈጣሪ ይፈታዋልና ከምእመናን የሚጠበቀው መታገሥ ብቻ ነው። ነገር ግን ይህ ጊዜ በብርቱ የምንፈተንበት ጊዜ መሆኑን አውቀን መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

ዋቤ መጻሕፍት

፩. ሃይማኖተ አበው፣ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፹፯ ዓ.ም አ.አ

፪. መልእክታተ ጳውሎስ (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፹፰ ዓ.ም አ.አ

፫. መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት፣ ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን) ፲፱፻፹፰ ዓ.ም አ.አ

፬. መንፈሳዊ ሕይወት ምንድር ነው? ማኅበረ ቅዱሳን ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች አ.አ ፲፱፻፺፮

፭. መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፸፮ ዓ.ም አ.አ

፮. መጽሐፈ ስንክሳር፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም አ.አ

፯. መጽሐፍ ቅዱስ ፲፱፻፹ ዓ.ም ናይሮቢ

፰. መጽሐፈ ቅዳሴ፣ (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፹፰ ዓ.ም አ.አ

፱. ክብረ ክህነት ሄኖክ ኃይሌ (ዲያቆን) አሰግ ሉሲ ማተሚያ ቤት አ.አ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

፲. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ጎርጎርዮስ (አባ) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፸፰ ዓ.ም አ.አ

፲፩. ድርሳን፣ ዮሐንስ አፈወርቅ (ቅዱስ) ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፹፯ ዓ.ም አ.አ

፲፪. ፍትሐ ነገሥት፣ (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፺፭ ዓ.ም አ.አ

www.zeyeneta.com

ከዚህ በፊት በአዘጋጁ ለንባብ የበቁ መጻሕፍት

፩. ትዳርና ተላጽቆ (ሩካቤ)

ገጽ ፻፵፯
ዋጋ ፲ ብር

፪ ሕይወተ ወራዙት (የወጣቶች ሕይወት)
ክፍል አንድ

ገጽ ፪፻፹፰
ዋጋ ፲፭ ብር

፫. ሕይወተ ወራዙት (የወጣቶች ሕይወት)
ክፍል ሁለት

ገጽ ፪፻፬
ዋጋ ፲፭ ብር

፬. ትምህርት ውግዘት

እግዚአብሔር ቢፈቅድ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚታተሙ

፭. ሕይወተ ወራዙት (ክፍል ሦስት)
፮. ጋብቻ ከማያምኑ ጋር

www.zeyeneta.com

በአዘጋጁ ለንባብ የቀረቡ መጻሕፍት

፩. ትዳርና ተላጽቆ
፪. ሕይወተ ወራዙት (ክፍል አንድ)
፫. ሕይወተ ወራዙት (ክፍል ሁለት)
፬. ትምህርተ ውግዘት

ከመጽሐፉ የተወሰደ

ዓላውያን (ወንጀለኞች) ነገሥታትና ሹማምንት አንድ ጊዜ በጥቅምና በሹመት በማታለል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በኃይልና በጉልበት በመደለልና በማስፈራራት ካህናትን የግል ፍላጎታቸው ማስፈጸሚያ ሲያደርጉ ኖረዋል። ስለዚህ ካህናት ምን ጊዜም ከሹማምንት ይልቅ ሰማያዊ ንጉሥን ብቻ መፍራት ይኖርባቸዋል። ‹‹እንደ ንጉሡ አሳንበሱ›› እንደሚባለው ጊዜ የወለደውን ንጉሥ የወደደውን በመከተል የማይወገዘውን ቢያወግዙ ወይም ደግሞ መወገዝ ያለበትን ሳያወግዙ ቢቀሩ በፈጣሪ ዘንድ እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ ሳይገሠጹ አይቀርም። ለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ ንጉሡ ዖዝያንን ባለመገሠጹ የደረሰበትን ማንሣት ብቻ በቂ ነው። (ኢሳ፮፡፩)

አስተያየት

ቤተ ክርስቲያንንና ትምህርቷን የማስተዋወቅ ሥራ የሁሉም ኦርቶዶክሳዊያን አገልጋዮች ኃላፊነት ቢሆንም ዘመኑን እየዋጁ ይህንን አደራ ለመወጣት የሚጣጣሩ ግን እጅግ ጥቂቶች ናቸው። ዲያቆን ጎብረት የሺጥላ በየዐውደ ምህረቱ ወቅታዊና ምላሽ በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ከማስተማሩም በተጨማሪ ሁላችንም በፈለግን ጊዜ ልናነበውና ልናስረዳው በምንችልበት መልኩ ይህንን አስረጅ ማዘጋጀቱ የቱን ያህል ኦርቶዶክሳዊ አደራውን እየተወጣ፣ ሌሎችንም ለመታደግ እየጣረ እንደሆነ ማሳያ ነውና የቤተ ክርስቲያናችን አምላክ በረድኤቱ ጠብቆ ለበለጠ ሥራ ያበቃው ዘንድ ምኞትና ጸሎቴ ነው።

ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ